# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ


## የሂዩማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
## የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


### የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

የሰዋስው ትምህርት አተገባበር ውጤታማነት ከተማሪዎች ቋንቋ ዳራ አንፃር

(በተመረጡ አስረኛ ክፍሎች ናሙናነት )


በ

መሰረት በላይ



መስከረም 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የሰዋስው ትምህርት አተገባበር ውጤታማነት ከተማሪዎች ቋንቋ ዳራ አንፃር

## (በተመረጡ አስረኛ ክፍሎች ናሙናነት )


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒተስ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጹሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር


በ

መሰረት በላይ



መስከረም 2016

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
## የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጹሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

**የሰዋስው ትምህርት አተገባበር ውጤታማነት ከተማሪዎች ቋንቋ ዳራ  አንፃር**

**(በተመረጡ አስረኛ ክፍሎች ናሙናነት)**

**በ**

**መሰረት በላይ**

| **የፈተና ቦርድ አባላት** | **ፊርማ** |
| --- | --- |
| --------------------------- | -------------------- |
| **የፈታኝ ስም** | **ፊርማ** |
| --------------------------- | -------------------- |
| --------------------------- | -------------------- |

## ምስጋና

ከሁሉም በማስቀደም የሆነው ሁሉ እንዲሆን ለፈቀደው ለልዑል እግዚአብሔር ያለኝን ከፍተኛ ክብርና ምስጋና  መግለጽ የሚችል አንደበት ባይኖረኝም የውስጤን ሁሉ መርምሮ የሚያውቅ አምላክ በመሆኑ ምስጋናዬ ከውስጤ ይድረሰው ፡፡ በመቀጠል ይህ ጥናት ይሳካ ዘንድ ወድ ጊዜያቸውን ሰውተው ጽሁፌን በማረምና አካሄዴን በማስተካከል በሁኔታዬ ሳይሰለቹ ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ አማካሪየ ዶክተር ሙሉሰው አስራቴ ከልብ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ፡፡

ለጥናቱ የሚያስፈልገኝን ወጭ በመሸፈን ትብብር ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ ፡፡

በመጨረሻም የድህረ ምረቃ ትምህርቴን እንድከታተል ላበረታታኝ ልጆቼን በመንከባከብ ድጋፉ ላልተለየኝ ባለቤቴ ዳንኤል ሀ/ማሪያም ልጆቼ ነብዩ ዳንኤል ፣ዮናታን ዳንኤል ፣ዮሴፍ ዳንኤል ምስጋናዬ የበዛ ነው፡፡ ሀሳብ በማካፈል ከጎኔ ሆናችሁ ላገዛችሁኝ ውድ እህቶቼ እና ወንደሜ አክብሮቴ ላቅ ያለ ነው ፡፡

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ


ምስጋና ....................iii
ማውጫ ....................iv
የሰንጠረዥ ማውጫ ....................vii
አጠቃሎ ....................viii
ምዕራፍ አንድ .................... 1
መግቢያ .................... 1
የጥናቱ ዳራ .................... 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት .................... 2
1.3 የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ .................... 2
1.4 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ .................... 2
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ .................... 2
1.6 የጥናቱ ወሰን .................... 3
1.7 የጥናቱ ውስንነት .................... 3
ምዕራፍ ሁለት .................... 4
ክለሳ ድርሳናት .................... 4
2.1 የሰዋስው ትምህርት ዝግጅት .................... 4
2.1.1 አላማ .................... 4
2.1.2 መልመጃ .................... 4
2.1.3 ትምህርቱን ማቅረብ .................... 4
2.2 የሰዋስው ትምህርት የማቅረቢያ ስልቶች .................... 5
2.2.1 ኢ-ርቱዕ ( Inductive ) የሰዋስው ማቅረቢያ ስልት .................... 5
2.2.2 ርቱዕ (Deductive ) የሰዋስው የማቅረቢያ ስልት .................... 6
2.3 የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ባህሪያት .................... 8
2.3.1 ግልፅነት (clear ) .................... 8
2.3.2 ብቁነት (Efficient ) .................... 8
2.3.3 አሳታፊ አስደሳችነት (Lively and interesting .................... 8
2.3.4 ተገቢነት (Appropriate ) .................... 9
2.3.5 አፍላቂነት (productive ) .................... 9

2.4 ሰዋስውን የማስተማር መርሆች ........ 9
2.5 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 10
ምዕራፍ ሶስት ........ 12
የአጠናን ዘዴ ........ 12
3.1 የጥናቱ ዘዴ ........ 12
3.2 የጥናቱ መረጃ ምንጮች ........ 12
3.3 የናሙና አመራረጥ ........ 12
3.3.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ........ 12
3.3.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ........ 12
3.3.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ........ 12
3.3.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 13
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 13
3.4.1 የሰነድ ፍተሻ ........ 13
3.4.2 የፅሁፍ መጠይቅ ........ 13
3.4.3 የክፍል ውስጥ ምልከታ ........ 14
3.4.4 ፈተና ........ 14
ምዕራፍ አራት ........ 15
የመረጃ ትንተና ........ 15
4.1 ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 15
የመምህራን የትምህርት ዝግጅት ........ 15
4.2 ለተማሪዎች ከቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 16
4.2.1 ዳራዊ ሁኔታ ........ 16
4.2.2 በሰዋሰው ትምህርት ዓላማ ላይ የተማሪዎቹ ግንዛቤ ........ 17
4.2 .3 የተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት ፍላጎት ........ 19
4.2.4 እርማት /ምጋቤ ምላሽ/ ........ 19
4.2.5 የፅህፈት ክሂል ልምምድ በተመለከተ ........ 20
4.2.6 መልመጃዎችን በተመለከተ ........ 21
4.2.7 ተማሪዎች መምህራን ሰዋስውን በምን መልኩ እንደሚያስተምሩ የሰጡት ምለሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 23
4.2.8 የመርጃ መሳሪያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ ........ 23

4.2.9 የሚቀረበው ሰዋስዋዊ ይዘት ካለችሁ ዳራዊ እዉቀት ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ በሚመለከት ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 24
4.2.10 መምህራን ተማሪዎቹን የማበረታታቸውን መጠን በተመለከተ ተጠኚ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 25
4.3 ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 25
4.3.1 የሰዋሰዉ ይዘቱን ለማቅረብ የተጠቀሙበትን አዉድ በተመለከተ ........ 25
4.3.2 ድጋፍ ሰጭ መሳሪያዎችን በተመለከተ ........ 26
4.3.3 ሰዋስው ይዘቱን ከተማሪዎች ዳራ ጋር ያለው ተጣጥሞሽ ........ 27
4.3.4 ምጋቤ ምላሽን በተመለከተ ........ 28
4.3.5 የተማሪዎች ተሳትፎ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 30
4.3.6 የቀረቡት ምሳሌዎችና መልመጃዎች ተግባቦትን ለማከናወን ያላቸው ሚና ........ 30
4.3.7 ለልምድ የቀረቡትን ብልሃቶች በተመለከተ ........ 31
4.3.8 በአፍልቆት ጊዜ የመምህሩን ጣልቃ ገብነት በተመለከተ ........ 32
4.4 የፈተና ውጤት ትንተና ........ 33
4.4.1. የምርጫ ጥያቄዎች ........ 33
4.4.2. ቃላትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ........ 34
4.4.3. ስረዓታቸውን የጠበቁ ሰዋሰዋዊ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት ........ 35
4.4.4. የሐረጎችን መሪ ቃል እና የሐረጎችን ዓይነት መጻፍ ........ 36
4.4.5. እማሪያዊ እና ፍካሪያዊ ፍቺ መስጠት ........ 37
4.4.6 የአማካይ ውጤቶች ንጽጽር ........ 37
ምዕራፍ አምስት ........ 40
ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች ........ 40
5.1 ማጠቃለያ ........ 40
5.2 የመፍተሄ ሃሳቦች ........ 41
ዋቢዎች ........ 43
አባሪ 1 በተማሪዎች የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ ........ 45
አባሪ ሁለት ........ 47
አባሪ 3 ፈተና አንድ ........ 49

## የሰንጠረዥ ማውጫ ገጽ

ሰንጠረዥ፡- 2 የተማሪዎች ዳራ ........ 17
ሰንጠረዥ ፡-3 በሰዋሰው ትምህርት ዓላማ ላይ የተማሪዎቹ ግንዛቤ ........ 18
በሰንጠረዥ፡-4 ተማሪዎቹ ሰዋስውን ትምህርት ለመማር ያላቸው ፍላጎት ........ 19
ሰንጠረዥ፡-5 መምህራን ለክፍል ስራና ለቤት ስራ የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ የሰጡት ን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 20
ሰንጠረዥ ፡-6 የፅህፈት ክሂል ልምምድ በተመለከተ በተመለከተ የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 21
ሰንጠረዥ ፡-7 የመልመጃዎቹን ክብደትና ቅለት በተመለከተ ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 22
ሰንጠረዥ:-8 የሰዋስው ትምህርት ይዘቱ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ያለው ቅንጅት በተመለከተ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 23
ሰንጠረዥ ፡-9 የመምህራንን የድጋፍ ሰጪ መሳሪያዎች አጠቃቀም የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 23
ሰንጠረዝ ፡-10 የሰዋስው ይዘቱ ከተማሪዎች ዳራ ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 24
ሰንጠረዥ፡-11 መምህራን ተማሪዎችን የማበረታታቸውን መጠን በተመለከተ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 25
ሠንጠረዥ፡-12 መምህራን የሰዋስውን ይዘቱን የተጠቀሙበት አውድ መጠን በተመለከተ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 26
ሰንጠረዥ፡-13 የመምህራን የደጋፍ ሰጪ መሳሪያዎች አጠቃቀም በተመለከተ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 27
ሰንጠረዥ ፡-14 የሰዋስው ይዘቱ ከተማሪዎች ዳራ ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ በተመለከተ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 28
ሰንጠረዥ፡-15 የመምህራናኑን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 29
ሰንጠረዥ :-16 የተማሪዎች ተሳትፎ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 30
ሰንጠረዥ ፡-17 መምህራን የሚያቀርቧቸውን ምሳሌዎችና ምልመጃዎች የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 31
ሰንጠረዥ፡-18 ለልምምድ የቀረቡ ብልሀቶች ተገቢነት የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 32
ሰንጠረዥ ፡-19 መምህራኑ በአፍልቆት ጊዜ የሚያደርጉት ጣልቃ ገብነት ደረጃ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 32
ሠንጠረዥ 20: የምርጫ ጥያቄዎች ውጤት ናሙና ቲ - ቴስት ........ 33
ሰንጠረዥ 21 : ቃላትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ውጤት ናሙና ቲ - ቴስት ........ 34
ሰንጠረዥ 22: ስረዓታቸውን የጠበቁ ሰዋሰዋዊ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት ውጤት ናሙና ቲ - ቴስት ........ 35
ሰንጠረዥ 23: የሐረጎችን መሪ ቃል እና የሐረጎችን ዓይነት መጻፍ ዉጤት ናሙናዎች ቲ - ቴስት ........ 36
ሰንጠረዥ 24: እማሪያዊ እና ፍካሪያዊ ፍቺ የመስጠት ውጤት ናሙና ቲ - ቴስት ........ 37
ሰንጠረዥ 25፡ የፈተና 1 እና ፈተና 2 ጥያቄዎች ውጤት ናሙናዎች ቲ - ቴስት ........ 38

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በወልቂጤ ከተማ ህዳሴ ፍሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሰዋስው ትምህርት አተገበባበር ውጤታማነት ከተማሪዎች ቋንቋ ዳራ አንፃር መፈተሽ ነው ፡፡ በወልቂጤ ከተማ ከሚገኙ አራት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዉስጥ በህዳሴ ፍሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአላማ ተኮር የናሙና ዘዴ የተመረጠ ሲሆን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጥቂት በመሆናቸው ሁሉም ተመርጠዋል እንዲሁም በብድግ ብድግ ናሙና ዘዴ የተመረጡ 120 ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ፣80 ተማሪዎች ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጓል ፡፡ ከእነዚህ መረጃ ሰጪዎች በሰነድ ፍተሽ ፣በፅሁፍ መጠይቅ ፣በክፍል ውስጥ ምለከታና በፈተና መረጃዎች ተሰብስበዋል ፡፡ የጠሰበሰቡት መረጃዎች አይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዘዴ በመጠቀም ተተንትነዋል ፡፡ በተጠቀሱት መሳሪያዎች በመታገዝ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተጠናክረው ባስገኙት ውጤት መሰረት የቋንቋ መምህራን የሰዋስው ትምህርት አተገባበር በሚመለከት በሰነድ ፍተሻ ፣በጽሁፍ መጠይቅ ፣በክፍል ምልከታና በፈተና አማካኝነት መረጃ ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎችም በማደራጀትና በመተንተን የሚከተሉትን ውጤቶች ለማግኘት ተችሏል ፡፡ መምህራኑ የሚዘጋጁበትን ይዘት ከተማሪዎቹ ዕድሜ የክፍል ደረጃና ከመጡበት ማህበረሰብ ጋር የመጣጣም አቅሙ አነስተኛ ሲሆን የዓላማ ዝግጅታቸውም የመስፋትና የተተግባሪነት ችግር ይታይበታል ፡፡ እንዲሁም መምህራን በአብዛኛው ርቱዕ ስልትን የሚጠቀሙ ሲሆን አተገባበራቸው አፍላቂና አሳታፊ አልነበረም ፣ የሰዋስው መዋቅርን ቅርፅ ፣ ፍቺና ማህበራዊ አጠቃቀም ለማስተማር በክፍል ውስጥና ውጭ ያሉ አውዶች የመጠቀም ልምዳቸው ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ ድጋፍ ሲጪ መሳሪያዎችን እንደማይጠቀሙ የጥናቱ ውጤት ያሳያል ፡፡ በተጨማሪም የመምህራኑ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ሰንመለከት ደግሞ በልምምድ ወቅት እርማት የሚሰጡ ቢሆንም የእርማት አሰጣጡ ግን ፊት ለፊት የተቀመጡና እጅ ያወጡ ተማሪዎችን ያማከለና ተዘውታሪነት የጎደለው ነበር ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛና በመማር ማስተማሩ ሂደቱም ላይ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል ፡፡ በሰዋስው ዕውቀት መመዘኛ ፈተና ላይም የጎላ ውጤት አልታየም ፡፡ በመሆኑም ከላይ ለተጠቀሱት አተገባባር ችግሮች የመፍትሄ ሀሳቦች በማስቀመጥ ጥናቱ ተጠናቋል ፡፡

## ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት ዋነኛ ዓላማ የተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎት ማጐልበት እና የሥነ-ጹሑፍና ሥነ-ልሳን (ሰዋስው )እውቀትን ማሳደግ ነው ።

የሰዋስው ምንነት አስመልክተው ባየ (2000፣xxi) ‹‹ሰዋስው የአንድን ቋንቋ ሥርዓት ከድምጽ አሰካኩ እስከ ሐረግ አመሰራረቱ ድረስ የሚያሳይ ሳይንስ ነው››በማለት ገልጸዋል ። ከዚህ ሀሳብ ጋር በተያያዘ ጌታሁን (1989 iv) ‹‹የቋንቋ ትምህርት ዓላማ በክሂሎች ላይ ብቻ ሳይሆን በሥርዓትም ላይ መሆን አለበት። ምክንያቱም ሁለቱም አንድ ቋንቋ ተማርኩ ከሚል ሰው የሚጠበቁ ችሎታዎች ናቸው። ይህ ካልሆነ ደግሞ ተምሬአለሁ የሚለው እውቀት ቁንጽል ይሆናል።›› በማለት ገልጸዋል ።

Ur (1988፣) በአንድ ቋንቋ የሰዋስው ችሎታ ከሌለ ወይም አጠቃቀሙን በአግባቡ ለይተን ካላወቅን የቋንቋ ችሎታችን ደካማ ወይም ጎደሎ እንደሚሆን አያጠያይቅም ሲሉ ገልጸዋል ። ከዚህ በተጨማሪ Ellis (2000) ይህንን ሀሳብ በመደገፍ የሰዋስው ትምህርት ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ባህሪያት በሚገባ ተረድተው በተግባቦት ሂደት ጥቅም ላይ የሚያውሉበትን ስርዓት የሚያሳይ እንደመሆኑ ሰዋስውና ተግባቦት ተነጣጥለው መታየት እንደሌለባቸው ይገልጻሉ።

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡትን ሀሳቦች ስንመለከት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ተማሪዎችን የታላሚውን ቋንቋ መዋቅራዊ ሥርዓት ተረድተው ቋንቋውን ለተግባቦት የሚያውሉበትን መንገድ ሲሆን በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር ወቅት ተማሪዎች በቋንቋ እንዲገለገሉበት ክሂልን ከሰዋስው ጋር አዋህዶ ማቅረብ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ነው።

እንደ Bygate et.al(1994) ገለፃ ሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለውን ስፍራ በተመለከተ ከአፍ መፍቻ ወይም ከሁለተኛ ቋንቋ ወይም ከውጭ ቋንቋ ጋር በተያያዘ መልኩ በትምህርት መሰጠት ‹‹አለበት/የለበትም›› በሚል ረገድ ብዙ ክርክሮች ሲደረጉ ቆይተዋል ። ይሁን እንጂ የሰዋስው ትምህርት በሁለተኛ ወይም በውጭ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ የትምህርቱ አብይ ጉዳይ ሆኖ ከመገኘት ያገደው ነገር የለም ።

ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትኩረት በተሰጠበት በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመንም ቢሆን በተለይም 1980ዎቹ ድረስ የሰዋስው ትምህርት የቋንቋ ትምህርት ማዕከላዊ ጉዳይ ሲሆን መቻሉን Michell (1994)፣ Rutherford (1987)፣ እና Tonkyn (1994) ይጠቁማል።

Brown (1994) የሰዋስው ትምህርትን አስፈላጊነት ሲጠቅሱ የቋንቋ ትምህርት የተማሪውን ክህሎት ከማዳበር ባሻገር ተማሪው ሊገነዘብ የሚገባውን ሰዋስዋዊ ዕውቀት ጭምር ማካተት ይኖርበታል ። ይህም የአፍ መፍቻ ቋንቋንም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋን በማስተማር ወቅት ከተግባቦት በተጨማሪ የአጠቃቀም ሥርዓቱን ማስተማር አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ የቋንቋ ዕውቀትና ችሎታ የሚለካው ተግባቦታዊ አገልግሎትን

ከስርዓቱ ጋር አቀናጅቶ በመገንዘብ በመሆኑ ሰዋስውን የማስተማር ተገቢነት መካድ የሌለበት መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

ከላይ የተገለጹት ማለትም የሰዋስው ትምህርት ለአጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት የሚያበረክተው አስተዋጾ ከፍተኛ እነደሆነ  ነው ፡፡

## 1.2  የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህ ጥናት እንዳዘጋጅ እንደምክንያት የሚጠቀሱት አነሳሽ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው ፡፡ አንድ የቋንቋ ተማሪ እንድን የቋንቋ ትምህርት ከተማረ በኂላ በቋንቋው መናገር ፣ማንበብ ፣ መፃፍና መስማት ይጠበቅበታል ፡፡ ነገር ግን አጥኚዋ በምታስተምርበት ትምህርት ቤት ዉስጥ በሰዋስው ትምህርት ላይ የተለያዩ ችግሮች ሲገጥማቸው አስተውላለች ፡፡ ምሳሌ ፡- የሀረጋትና የዐ.ነገሮች አለመጣጣም ክፍተቶች ይጠቀሳሉ ፡፡ በዚህ ምንያት በተለያየ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት አተገባበር ውጤታማነታቸውን  መፈተሽ አስፈላጊ በመሆኑ በዚህ ርዕስ ላይ ጥናት እንድታካሄድ አነሳስቷቷል ፡፡

## 1.3 የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ

የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ በጉራጌ ዞን በወልቂጤ ከተማ በህዳሴ ፍሬ 10ኛ ክፍል ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አተገባባር ውጤታማነት ከቋንቋ ዳራ አንጻር በመገምገምና በትምህርቱ አተገባባር ላይ የሚታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመለየት ፣ደካማ ጎኖቹን የሚወገዱባቸውን የመፍትሔ አቅጣጫዎችን መጠቆም ነው ፡፡

## 1.4 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ

ከዚህ በላይ የተገለጸውን የጥናቱን አጠቃላይ አላማ ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ የተተኮረባቸው ዝርዝር ዓላማዎች ተነድፈዋል ፡፡እነዚህም ዝርዝር ዓላማዎች ከዚህ በታች የቀረቡት ናቸው ፡፡

- የቋንቋ መምህራኑየትምህርት ዝግጅት ውስጥ የተገለጹ ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት ዓላማዎች አጠቃላዩን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከማሳካት  አንፃር ተገለጹ መሆናቸውን መገምገም ፡፡
- በክፍል ውስጥ የመማር የማስተማር ክንውን የቋንቋ መምህራኑ ሰዋሰዋዊ ይዘቶችን የሚያቀርቡባቸው መንገዶች መገምገም ፡፡
- ተማሪዎች ሚቀርቡላቸውን የሰዋስው ይዘቶች የሚማሩበትና የሚለማመዱባቸውን ስልቶች መገምገም ፡፡
- ተማሪዎች ለሰዋስው ትምህርት ያላቸው ፍላጎት መፈተሽ ፡፡
- መምራኑ የሚያቀርቡበት ሰዋሰዋዊ ይዘት ተማሪዎች ካላቸው ዳራዊ ዕውቀት ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ መፈተሽ መገምገም ፡፡
- በሰዋስው ትምህርት አተገባባር ውጤታማ መሆን አለመሆን መገምገም

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ከዚህ ጥናት የሚገኘው ውጤት አማርኛን በማስተማር ሂደት የቋንቋው ተማሪዎች የታቀደላቸውን የሰዋስው ትምህርት በአግባቡ ተምረው ውጤታማ እንዲሆኑ ፡፡

- ✓ በክፍል ውስጥ ሰዋስው ከቋንቋ ኪሂሎች ጋር እንዴት በቅንጅት መቅረብ እንዳለበት ለአማርኛ መምህራን አቅጣጫ የመጠቆም ፋይዳ ይኖረዋል ፡፡
- ✓ የሰዋስው ትምህርት ለቋንቋ ኪሂሎች ጋር ተቀናጅቶ የሚቀርብበትን ብልሃት በመጠቆም ረገድ አስተዋጾ ያደርጋል ፡፡
- ✓ በአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት ላይ የበለጠ ተጠቃሚ የሚሆነውን በመለየት ትምህርቱ በምን አይነት ዘዴ መሰጠት እንዳለበት ይጠቁማል ፡፡
- ✓ በዚህ ርዕስ ዙሪያ ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ ሌሎች አጥኚዎች እንደ መነሻ ሆኖ ያገለግላል ፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በወልቂጤ ከተማ ከሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርተ ቤቶች ውስጥ የህዳሴ ፍሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ብቻ ነው ፡፡ ጥናቱን ለማድረግ ካላት አቅም ፣ጊዜና ወጪ አንፃር ሁሉንም በጥናቱ ማካተት ከባድ በመሆኑ በአንድ ትምህርት ቤት ላይ ብቻ አትኩራለች ፡፡ በናሙናነት የተወሰደው ትምህርት ቤት ከዘጠንኛ እስከ አስራሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚማሩበት ሲሆን በዚህ ጥናት የተካተቱት ግን የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች እና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው ፡፡ ጥናቱ በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚያስተምሩ የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራንን የሰዋስው ትምህርት ሲያስተምሩ አቀራረባቸው እንዴት እንደሚተገብሩት መፈተሽ ላይ የተገደበ ነው ፡፡ እንዲሁም ይህ ጥናት የቋንቋ ኪሂሎችን እና ሌሎች ክፍሎች አይፈትሽም ፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውስንነት

አጥኚዋ በጥናቱ ሂደት በርካታ ውስንነት ያጋጠሟት ሲሆን ፣ ከእነዚህ መካከል አንዳንድ መረጃዎችን የሚያቀርቡ ተጠኚዎች መረጃዉን በአግባቡ ሞልተው ለመመለስ ፍቃደኛ አለመሆን ፣በፈተና ቀን አለመገኘትና ፈተናውን ለማረም በቂ ጊዜ አለመኖር የመሳሰሉት ውስንነቶች ተጠቃሽ ናቸው ፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

### 2.1 የሰዋስው ትምህርት ዝግጅት

መምህራን የሰዋስው ትምህርትን ክፍል ውስጥ ከማስተማራቸው በፊት የሰዋስው ትምህርቱን ማዋቀርና በውስጡ ስለሚያካትታቸው ይዘቶች ሊያውቁ ይገባል ። ምክንያቱም አንዳንድ መዋቅሮች ከተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር የሚመሳሰሉና በቀላሉ ሊታወቁ የሚችሉ ሲሆኑ አንዳንዱ ደግሞ ሙሉ በሙሉ የተለያዩና ተማሪዎቻችን ቶሎ ሊገነዘቧቸው የማይችሉ ይሆናሉ ። በመሆኑም መምህራን የሰዋሰው ትምህርቱን ክፍል ውስጥ ከማቅረባቸው በፊት በቂ ጊዜ ወስደው ሊዘጋጁበት ይገባል (Ur 1988፣5) በዝግጅት ወቅትም የሚከተሉት ነጥቦች ከግምት ማስገባት ይኖርባቸዋል ።

**2.1.1 አላማ ፡-** ማንኛውም መምህር አንድን የትምህርት ይዘት ሲያዘጋጂ ከትምህርቱ በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቀውን ግልጽ አላማ ማስቀመጥ ይኖርበታል ። በመሆኑም የሰዋስው ትምህርት ዋና አላማ ተማሪዎቹ ተግባቦታዊ ተግባራትን እንዲያከናውኑ የሚያደርግ መሆን አለበት ። ይሁን እንጂ የሰዋስው ትክክለኛነት ላይም በተወሰነ መልኩ ማተኮር አለበት ይህንን አስመልክቶ Grant(1987) ፣ Ur(1988) የሰዋስው ልምምድ ተፈላጊውን የቋንቋ ትምህርት ዉጤት ሊያስገኝ የሚችለው ልምምዱ በሰዋስው አላማዎች መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ እንደሆነ ነው ይላሉ ። በመሆኑም መምህራን የሰዋስው ትምህርቱን ሲያዘጋጁ ሁለቱም ከግምት ውስጥ አስገብተው ግልጽ አላማ ሊያስቀምጡ ይገባል።

**2.1.2 መልመጃ ፡-** በዚህ ደረጃ መምህሩ ለተማሪዎች ያቀረበላቸውን አዳዲስ የሰዋስው ይዘቶች በማዳመጥ ወይም በሌላ አይነት መንገድ በመለማመድ በይዘቶቹ መገልገል እንዲችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ። ተማሪዎቹም የቀረበላቸውን አዲስ የቋንቋ መዋቅር በተግባቦታዊ ሂደት ልምምድ አማካኝነት እንዲያሰርፁና ከክፍል ውጭ ባለው አውድ እንዲገለገሉበት ይጠበቃል (Grant፣1987)።

**2.1.3 ትምህርቱን ማቅረብ ፡-** ይህ መረጃ መመምህሩ ተማሪዎቹ እንዲማሩ የተወሰነውን ተገቢ ይዘት፣ ለምሳሌ ፡- አዲስ የቋንቋ ይዘቶች ፣የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ አገልግሎት ወይም መዋቅራዊ አደረጃጀት ግልፅ በሆነ አውድ ወይም በምሳሌ በማስደገፍ በገለፃ የሚያቀርቡበት ነው። (Grant፣1987)

- **መግቢያ** ፡- መምህሩ የሚያቀርበውን ትምህርት የትምህርቱን ዓላማ ለተማሪዎች የሚያሳውቅበት ፣ተማሪዎች በተለያዩ የትምህርት እርከኖች ማከናወን የሚገባቸውን ተግባራት የሚገልፅበት ክፍል ነው ። በቀዳማዊ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ያቀረበውን ትምህርት ዋና ዋና ይዘቶች ፣ቃላትን ፣ሰዋሰዋዊ መዋቅሮችን ወዘተ… የሚከልስበት ደረጃ ነው ። ይህ ደረጃ ለሚቀርበው ትምህርት ወሳኝ የሆኑ አዳዲስ ቃላትንም ለማስተማር አመቺ ጊዜ ነው (Ur፣1988 ፣ Grant፣1987)።
- **የጽሁፍ ማጠናከሪያ መልመጃ** ፡- በዚህ ደረጃ ተማሪዎቹ በተለያዩ መልኮች ልምምድ ያደረጉባቸውን አዳዲስ የሰዋስው ይዘቶች በጹሑፍ መልክ እንዲለማመዱባቸው

ያደርጋል ። የጹሑፍ ማጠናከሪያ መልመጃው ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን አዲስ የቋንቋ መዋቅር እንዲያስታውሱ ይረዳቸዋል ። በመሆኑም በትምህርት ዝግጅት ወቅት ተማሪዎች የጽሑፍ ማጠናከሪያ መልመጃዎች ሊገለፁ የሚገባ ሌላው ጠቃሚ የዝግጅት አካል ነው(Grant፣1987) ።

- **ድጋፍ መሳሪያዎች** ፡- ተማሪዎች አንድን ትምህርት በቀላል እንዲረዱትና ከራሳቸው ጋር እንዲያዋህዱት የደጋፊ መሳሪያዎች ሚና ከፍተኛ ነው ። ይህንንም ለማድረግ መምህራን ደጋፊ የሆኑ ስዕላዊ መረጃ መሳሪያዎች ወይም ምንባቦች ፣ ሰንጠረዥ ወዘተ…ሊጠቀሙ ይችላሉ ። በመሆኑም መምህራን በሰዋስው ትምህርት ዝግጅት ወቅት ደጋፊ መሳሪያዎች ላይም ትኩረት ሊሰጡ ይገባል (Cunning swoth 1984፣50) ።

## 2.2 የሰዋስው ትምህርት የማቅረቢያ ስልቶች

የአንድን ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለማቅረብና በሱም አማክኝነት ተማሪዎች ስለቋንቋው እንዲያቁና እንዲጠቀሙ ለማድረግ የተለያዩ ማቅረቢያ ስልቶች አሉ ። እነዚህን ማቅረቢያ ስልቶች የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ይከፍሏቿል ። ለአብነትም Harmer(1987፣3) በሁለት ሲከፍላቸው ፣ እነርሱም ግልፅ (Covert) እና ሽሽግ (Covert) ናቸው ። ማረው (1998፣52) widodo (2006) ፣ Celce-Moria (1991፣229) እና Cunng Sworth(1984፣32) ቀጥተኛ (Deductive) እና (inductive ) በማለት በሁለት ይከፍላቸዋል። በተጨማሪም Atkins et.al (1995፣8) ደግሞ ጥቅል ቀደምና ዝርዝር ቀደም በማለት አሁንም በሁለት ይከፍላቸዋል ። በአጠቃላይ ግን የሁሉንም ምሁራን አከፋፈል ስንመለከት በስያሜ ተለያይተው በሀሳብ ግን ተመሳሳይ እንደሆኑ ነው። በመሆኑም ለአሰራር ያመች ዘንድ ርቱዕ እና ኢ-ርቱዕ የሚለውን ስያሜ ለመጠቀም እንሞክራለን።

### 2.2.1 ኢ-ርቱዕ ( Inductive ) የሰዋስው ማቅረቢያ ስልት

ይህ የማቅረቢያ ስልት በበርካታ ባለሙያዎች ዘንድ የህግጋት ምርምር ትምህርት (Rule-discovery learning) የሚል ስያሜ ተሰቶታል ። ፅንስ ሃሳቡም በርካታ ዝርዝር ነገሮችን በመመልከት በነዚያ ነገሮች አማካኝነት አጠቃላይ መርህን ወይም ህግን ማውጣት ማለት ነው Widodo (2006) ::

በዚህ ማቅረቢያ ስልት የቋንቋውን ሰዋስው ህጎች በቀጥታ ለተማሪዎች አይቀርቡም ። ይልቁንም ስልቱ የሚጀምረው መምህራን ለተማሪዎች የተለያዩ ምሳሌዎችን ይሰጡና ተማሪዎች ከምሳሌዎች ውስጥ የሰዋስው ህግጋትን በማውጣት ነው ። በመቀጠልም መምህሩ የሰዋስውን ህግጋት በቃል ወይም በፁሑፍ ለተማሪዎች ያቀርባል (Harmer 1987፣29 Widodo 2006 ፣ Cunning sworth 1984፣32) ። ይሁንና በዚህ የማቅረቢያ ስልት የሚቀርቡት የሰዋስው ህግጋት ትንታኔ አነስተኛ ሲሆን ተማሪዎች ከምሳሌው ተነስተው በጥልቀት ተመራምረው ህግጋቱን ያጠናሉ ።

የሰዋስው መዋቅሮችን በዚህ ስልት ስናቀርብ ተማሪዎች ተሳታፊ በመሆን ምክንያታቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግና ሙሉ ትኩረታቸውን የሚስብና የማሰብ አቅማቸውን እንዲጠቀሙ የሚያስችል የትምህርት ይዘትን ማቅረብ ይኖርበታል ። በተጨማሪም የማስተማር ስልታችን በይበልጥ ተማሪ ተኮር የሆነና መምህሩ ለሰዋስው ህግጋት ጣልቃ ገብቶ ማብራሪያ የማይሰጥ መሆን አለበት (Harmer 1987፣29) ።

ኢርቱዕ የማቅረቢያ ስልት የራሱ የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት በመሆኑም እነዚህን ጠንካራና ደካማ ጎን ቀጥለን እንመለከታለን ።

**ጠንካራ ጎን**

- ❖ ተማሪዎች ከሚሰጧቸው ምሳሌዎች ተነስተው ህግጋቱን እንዲያወጡ ያግዛል በዚህም በነፃነት የመማርና በራስ የመተማመን ችሎታቸውን ያዳብራል ።
- ❖ ተማሪዎች አዕምሯቸውን በስፋትና በጥልቀት እንዲጠቀም ይጋብዛል በተጨማሪም የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ህግጋት ከራሳቸው ጋር እንዲያዋህዱና ቶሎ እንዲያስታውሱ ያደርጋል ።
- ❖ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ በስፋት ስለሚሳተፉ የመማር ፍላጎታቸው ያነሳሳል ።
- ❖ የተማዎችን የርስ በርስ መስተጋብር ስለሚፈቀድ ለቋንቋ ኪሂሎች መዳበር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ።
- ❖ የተማሪዎች ችግር የመፍታት ችሎታ ያዳብራል ።
- ❖ በነገሮች መካከል ያለን እንድነትና ልዩነት ለመረዳት ይጠቅማል (Widodo 2006 ፣ ማረው 1998)።

**ደካማ ጎን**

- ❖ ጊዜን ጉልብት ያባክናል
- ❖ መጀመሪያ ላይ የሰዋስው ህግጋት በጥልቀት ለተማዎች ስለማይቀርቡ ተማሪዎች ወደ ተሳሳተ ግንዛቤ እንዲያመሩ ሊያደርግ ይችላል ።
- ❖ ከዚህ በፊት የህግጋት ትንታኔ ቀርቦ መማር የለመዱ ተማሪዎችን ግራ ሊያጋባቸው ይችላል (Windodo 2006)።

## 2.2.2 ርቱዕ (Deductive ) የሰዋስው የማቅረቢያ ስልት

በዚህ ስልት መጀመሪያ የሰዋስው ህግጋት ፣ መርህ ፣ንድፈ ሀሳቦች ይቀርቡና መልመጃዎች መጨረሻ ላይ ይመጣሉ ። በመሆኑም ስልቱ ከአጠቃላይ ተነስተን ወደ ዝርዝር እንድንሄድ የሚያደርግ ነው ይህ የማቅረቢያ ስልት ለበርካታ ዘመናት በተለያዩ መማሪያ መጻሕፍት ላይ ሲተገብሩ የኖረ ነው ። በርቱዕ የማቅረቢያ ስልት ህግጋት ለተማሪዎች ይቀርባል ። ማለትም በእያንዳንዱ መዋቅር የቅርጽ ልዩነት ላይ ግልጽ ትንተና በማድረግ የሚቀርብ ነው ። የሚቀርበው የሰዋስው ትምህርት አላማም ተግባቦትም ማከናወን ሳይሆን ተማሪዎችን የታላሚውን ቋንቋ የቃል ክፍሉን ፣ሀረጋትንና ዐ.ነገሮችን እንዲለዩ ማስቻል ነው ። በዚህ ስልት እንዳንዴ ተማሪዎች ትግባቦት የሚያከናዉኑበት አጋጣሚ ቢኖርም ተማሪዎች ስህተት እንዳይሰሩ መምህሩ ጣልቃ በመግባት ቁጥጥር ሊያደርግና ምጋቤ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል (Harmer 1987፣4 Widodo 2006 ፣ Cunning sworth 1984፣32፣33) ።

በዚህ የማቅረቢ ስልት መምህራን የሰዋስው መዋቅርን በሚያቀርቡበት ወቅት ሊከተሏቸው የሚገቡ መርሆችን Widodo (2006)፣Tho mburk (1999፣32)ን በመጥቀስ እንደሚከተለው አስቀምጠዋል ።

1. የሚቀርቡት ህግጋት እውነተኛ ትክክለኛ መሆን፣
2. ህግጋቱ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ቅርጽ ተጠቅመው ተግባራዊ የሚያደርጉትን ገደብ በግልጽ የሚያሳዩ መሆን፣
3. ህግጋቱ ግልፅ ፣ቀላልና የማያሻማ መሆን ፣
4. ህጋቱ ተማሪዎችን ከዚህ በፊት ከሚያውቁት ነገር ጋር ተያይዘው መቅረብ፣
5. ህግጋቱ የተገቢነት ደረጃን የጠበቀ መሆን፣
6. ህግጋቱ በምሳሌ የተደገፉና የተማሪዎችን የመረዳት አቅም ያገናዘቡ መሆን አለባቸው፡፡

ርዕቱ የማቅረቢያ ስልት ልክ እንደ ኢ-ርቱዕ የማቅረቢያ ስልት የራሱ የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት ፡፡

ጠንካራ ጎን

- የሰዋስው ህግጋቱን በቀጥታ የሚያቀርብ በመሆን ሰአት ይቆጥባል፣
- ህግጋቱን ከተረዱ በኂላ ምሳሌ ያቀርባሉ፣
- የማገናዘብ ችሎታ ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎችን የመማር ስልት ያጠናክራል፡፡

ደካማ ጎን

- የሰዋስው ትምህርት አቅርቦት መምህር መራሽ በመሆኑ የተማሪዎችን ተሳትፎና የእርስ በርስ ግንኙነት ይቀናሳል ፡፡
- የህግጋቱ ገለፃ በተግባቦት ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ እምብዛም የሚታወስ አይደለም ፡፡
- የማቅረቢያ ስልቱ ‹‹ቋንቋን መማር ማለት ህግጋት ማወቅ ነው ›› የሚለውን አመለካከት የሚያበረታታ በመሆኑ ለተግባቦት ቦታ አይሰጥም (Widodo ፣2006) ፡፡

ከሁለቱ የማቅረቢያ ስልቶቸ ተመራጭ የሆነው የቱ  ነው ? ለምን ? ለነዚህ ጥያቄ የተለያዩ ምሁራን ሀሳባቸውን አስቀምጠዋል ፡፡ በመሆኑም ቀጥለን የትኛው ስልት ተመራጭ እንደሆነና የትኛውን መጠቀም እንዳለብን ለማየት እንሞክራለን ፡፡

ከሁለቱ የማቅረቢያ ስልቶች አንዱን መርጦ ለመጠቀም የተማሪዎች ዝንባሌ ይወስናል፡፡ በተለይም የተማሪዎችን እድሜ ፣ የትምህርት ደረጃ ከግምት  ውስጥ መግባት አለበት ፡፡ ይኸውም ተማሪዎቻችን ወጣትና ለአቅመ አዳም የደረሱ ከሆነ መደበኛ የሰዋስው ህግጋትን የመረዳት አቅም ይኖራቻዋል ፡፡ ህፃናት ከሆኑና የማገናዘብ አቅማቸው አነስተኛ ከሆነ የሰዋስው ህግጋቱን በማስወገድ የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት ብናስተምር ተመራጭ ነው (Mahmood salimi (2008) ::

በተጨማሪም Ellis (2006) ጀማሪ ተማሪዎች ስለታላሚው ቋንቋ ሰዋስው ህግጋት የሚኖራቸው እውቀት አነስተኛ ስለሆነ ሰዋስውን መማር ያለባቸው ክሂል ተኮር (Task based) በሆነ መንገድ ነው ፡፡

እንደ Mirosolow (2004) ደግሞ ኢ-ርቱዕ ተመራጭ የማቅረቢያ ስልት ነው ፡፡ ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት ትምህርቱን አይረሴና ትርጉም ያለው ከማድረጉም በተጨማሪ

ተማሪዎች በቡድን እንዲሰሩ በመጋበዝ በነፃነት የመማር እድላቸውን ከፍ ስለሚያደርግ የሚለውን ነው ፡፡ ይህንና ኢ-ርቱዕ የማቅረቢያ ስልት ብዙ ሰአት የሚጠይቅ በመሆኑና ለሁሉም የሰዋስው አይነቶች አመቺ ባለመሆኑ ሁሌም መጠቀም አይቻልም ይላሉ ፡፡

በመሆኑም ኢ-ርቱዕ ተመራጭ ቢሆንም ለሁሉም ተማሪና የክፍል ደረጃ የመሆን አቅሙ አነስተኛ ስለሆነ ሙሉ ለሙሉ እሱን ብቻ መጠቀም አዳጋች ነው ፡፡ ለዚህም ነው Harmer (1987፣30) አ-ርቱዕ የማቅረቢያ ስልት በማንኛውም አጋጣሚና ለሁሉም የክፍል ደረጃ ላሉ ተማሪዎች ላይመች ይችላል ፡፡ ይኸውም ስልቱ ረዥም ሰዓት የሚወስድና አንዳንድ ጊዜም አወዛጋቢ ስለሚሆን መምህራን ስልቱን መቼ፣ለየትኛዎቹ ተማሪዎች በየትኛው ሰዋስው አይነት ላይ መጠቀም እንዳለባቸው መወሰን አለባቸው የሚሉት ፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ ሁለት የማቅረቢ ስልቶች የራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎን አላቸው ፡፡ በመሆኑም መምህራን ከሁለቱ የማቅረቢያ ስልቶች አንዱን ከሌላው አማርጠው ወይም በጥምረት መጠቀም ይችላሉ ፡፡ ይህንና እንዱን ከሌላው አማርጠው ወይም በጥምረት ለመጠቀም ተማሪዎቹና ለትምህርት የሚቀርበው የሰዋስው ይዘት ይወስናል ፡፡ ይኸውም ተማሪዎቹ በለጋ እድሜ ያሉና በዳራዊ ልምዳቸውም አነስተኛ ከሆኑ ያለ ሰዋሰዋዊ ህግጋት ትንታኔ የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት ማስተማር በቋንቋ ትምህርት ላይ በጥልቀት የማሰብ ክህሎታቸውን ስለሚያሰፉ ኢ-ርቱዕ የማቅረቢያ ስልትን ተጠቅሞ ማስተማር ውጤታማ ነው ፡፡

በሌላ በኩል አዋቂዎች ከሆኑና ከተለያዩ የሙያ መስኮች ጋር ትውውቅና ብስለት ያላቸው ተማሪዎች የሰዋስው ህግጋትን ከመምህሩ ይጠብቃል ፡፡ በመሆኑም ለነዚህ ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርቱን ርቱዕ የማቅረቢያ ስልትን ተጠቅሞ ማቅረብ ውጤታማ ነው ፡፡

### 2.3 የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ባህሪያት

የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ክፍል ውስጥ ርቱዕም ሆነ ኢ-ርቱዕ የማቅረቢያ ስልት ተጠቅምን ስናቀርብ የሚከተሉትን አምስት ባህሪያት የሚያሟላ ከሆነ የምናስተምረው ሰዋስው ተማሪዎቻችን ትምህርቱን ከተማሩ በኋላ የምንጠብቀው ውጤት እንደምናገኝ Harmer (1987፣18)ይገልፃል ፡፡ እነዚህም ጥሩ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ባህሪያት ፦

**2.3.1 ግልፅነት (clear )** ፦ የሰዋስው ትምህርት ለተማሪዎች በምናቀርብበት ወቅት ተማሪዎቹ የቀረበበትን ሁኔታ ከመረዳት እንፃር ግራ መጋባት የለባቸውም ፡፡ በተጨማሪም የቀረበውን ቋንቋ ምንነት በግልፅ መረዳት መቻል አለባቸው ፡፡ በመሆኑም የሚቀርበው ሰዋስው ይዘት ገለፃ ፣ምሳሌ፣ትዕዛዝ ፣መልመጃ ግልፅ ሊሆን ይገባል ፡፡

**2.3.2 ብቁነት (Efficient )** ፦ የሰዋስው ትምህርት አላማ ተማሪዎች የሚማሩትን ቋንቋ ህግጋትና መዋቅር ተጠቅመው ተግባቦትን እንዲፈፅሙ ማድረግ ነው። ይህንንም ለማድረግ የሚቀርበው ሰዋስው በቂና ተማሪዎች በደረጃቸው መጠቀም ያለባቸው ቋንቋ እንዲያፈልቁ የሚያስችል መሆን አለበት።

**2.3.3 አሳታፊ አስደሳችነት (Lively and interesting )** ፦ በጥሩ የመማር ሁኔታ እና በአሳታፊ የመማር ማስተማር ሂደት የሚሰጥ የቋንቋ ትምህርት አይረሴ ነው። ይህም

በመሆኑ ተማሪዎች የተማሩትን ቋንቋ የማስታወስ ችሎታቸው ከፍተኛ ነው ። በመሆኑም የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ አሳታፊና አስደሳች መሆን አለበት ።

**2.3.4 ተገቢነት (Appropriate )** ፡- የምናስተምረው ሰዋስው ምን ያህልም አስደሳች እና ስሜት ሳቢ ቢሆንም ለቋንቋው ግን አስተዋፆ ያለው ተገቢ መሆን አለበት ። በሌላ አገላለጽ የሚቀርበው ነገር ስለሰዋስው ምንነትና  አጠቃቀም የሚያሳይ መሆን አለበት ።

**2.3.5 አፍላቂነት (productive )** ፡- የሚቀርበው ስዋስው ተማሪዎች የሚማሩትን ቋንቋ ተጠቅመው በርካታ ዓረፍተ ነገሮችን እና ጥያቄዎችን እንዲመሰርቱ የሚያደርግ መሆን አለበት ።

## 2.4 ሰዋስውን የማስተማር መርሆች

መምህራን የሰዋስው ትምህርትን ፣መዋቅር ለተማሪዎች በሚያስተምሩበት ወቅት የሚከተሉት ነጥቦች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል ።

1. ተማሪዎች አንድን የሰዋስው መዋቅር እንድ ጊዜ ብቻ በመማር ሁሉን ነገር መያዝ አይችሉም ። የአንድን መዋቅር ትክክለኛ (ተገቢ) ቅርፅ፣ ፍቺና ማህበራዊ አጠቃቀም በተሟላ መልኩ ለመጠቀም የሚችሉት በሂደት በሚመጣ እዉቀት ነው። ስለዚህም እንድን መዋቅር አንድ ጊዜ ከማስተማር ይልቅ በተለያዩ ጊዜያት በመደጋገም ማስተማር ይኖርባቸዋል ( clece - nurica 1991፣284፣ free man 1997) ።

2. ሰዋስውን ስናስተምር  የመጨረሻው ግብ ስዋስው መሆን የለበትም ። ይልቁንም ተማሪዎች የቋንቋውን ትርጉም ፣ማህበራዊና ባህላዊ አጠቃቀም፣ዲስኩር፣ስነልሳናዊ አገባብ፣ወዘተ... ያቁ ዘንድ ነገሮች ጋር በማቀናጀት ማስተማር አለበት ( clece -muricia 1991፣466-67)።

3. ተማሪዎች የአንድን ቋንቋ መዋቅር ህግ ሲማሩ ያህግ የማይሰራባቸውንም አጋጣሚ ( Exception ) ማወቅ አለባቸው ። ካልሆነ ግን ስህተት ላይ ሊወድቁ ይችላሉ (clece - nurica 1991፣284) ምሳሌ የአማርኛ ስሞች ለብዙ ቁጥር ሲረቡ ‹‹ኦች››ን ለብዙ ቁጥር አመልካችን ይጠቀማሉ። ይሁንና የአማርኛ የብዙ ቁጥር አመልካች ምዕላድ ‹‹ኦች›› ብቻ ሳይሆን ስሞች በአናባቢ ድምጽ የሚጨርሱ ከሆና ‹‹ዎች››ን ለብዙ ቁጥር አመልካችነት ያስከትላሉ ።

4. የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ወዳላቸው እውቀትና ልምድ ያዘነብላሉ ። ይኸውም ተማሪዎቹ  የሰዋስው ትምርቱን ጀማሪ ከሆኑ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ላይ ያለው ህግ ለሁለተኛ ቋንቋውም እንደሚሰራ አድርገው ሊቆጥሩ ይችላሉ። ነገር ግን በሁለተኛ ቋንቋ ሳዋስው እውቀት ካላቸው የታላሚ ቋንቋ ህግጋት ላይ ትኩረት ያደርጋል ። ስለዚህ መምህሩ ይህን ለይቶ በማወቅ ሁሉንም የመዋቅር ጉዳዮች በቡድን በተመሳሳይ ሁኔታ ለማስተማር ከመሞከር ይልቅ ተማሪዎቹ ከሚያቁት ወይም ከደረሱበት የመዋቅር እውቀት መነሳት አለበት ። ይህ ሁኔታም ከክፍል ክፍል የሚሰጠውን የመዋቅር ትምህርት እንዲለያይ ያደርገዋል ። የልዩነቱም መንስኤዎች ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋው ላይ ያላቸው ዳራዊ እውቀትና በታላሚው ቋንቋ ያላቸው እውቀት ነው (celce-Muricia 1991፣284)።

5. ቋንቋ ዉስብስብ በመሆኑ መምህራን በተለያዩ የሰዋስው ይዘቶች የተለያዩ የማስተማር ስልቶችን ቢጠቀሙ ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋን ሰዋስው በጥሩ ሁኔታ መርዳትና መጠቀም ይችላሉ (celce-Muricia 1991፣284)።

## 2.5 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

የሰዋስው ምንነት አስመልክተው የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ብያኔዎች ሲሰጡ ይታያሉ ከተገለጹት ብያኔዎች መካከል የተወሰኑትን ለማየት ተሞክሯል ።

በዚህም መሰረት በየጊዜው በሰዋስው ትምህትና በቋንቋ ማስተማር ላይ ያተኮሩ ጥናቶች ይካሄዳሉ ። በአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት ላይም እንዲሁ ጥቂት ጥናቶች ተደርገዋል ፤ ይደረጋሉም ። ለአብነትም እስሌማን (2003) ፤በላይነህ (2003)፤ ህልፍቲ (2004) መጥቀስ ይቻላል።

እስሌማን (2003) ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ባቀረበው ጥናት በአስራ ሁለተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከግልፅነት ፣ ከትክክለኛነት ፣ከተገቢነት ፣ከተከታታይነት ፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት እንዲሁም የተማሪዎችን ትምህርት ዳራ ከማገናዘብ አንፃር ጥሩ ገጽታ ያላቸው ሆነው መገኘታቸውን አሳይቷል ። ሰዋስዋዊ የዘቶች የታላሚውን ቋንቋ ቅርጽ የሚተነትኑ እንጂ ለመዋቅሩ ፍቺ ትኩረት ያላደረጉ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤቶች አመላክቷል።

በላይነህ (2003) ‹‹የሰዋስው ትምህርት አተገባበር (በሀድያ ዞን በተመረጡ ሶስት የስምንተኛ ክፍል ትምህርት ቤቶች ናሙናነት››)በሚል ርዕስ በሌሞ ወረዳ ካሉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአምቤቾ ጎዴ፣ለሬባና በሌሶ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጥናት ያደረገ ሲሆን የጥናቱ ግኑኝነት መምህራን ከሚያዘጋጁበት ይዘት ፤ተማሪዎች ዕድሜን፤የክፍል ደረጃና ከመጡበት ማህበረሰብ ጋር የመጣጣሙ አቅም አነስተኛ ሲሆን የዓላማ ዝግጅታቸውን የመስፋትና የተግባራት ችግር ይታይበታል እንዲሁም መምህራኑ በአብዛኛው አተግባበራቸው አሳታፊ አልነበረም ሰዋስውን መዋቅርን ቅርፅ ፤ፍቺና ማህበራዊ አጠቃቀም ለማስተማር በክፍል ውስጥ ና ውጭ ያሉ አውዶችን የመጠቀም ልምዳቸው አነስተኛ ከመሆኑም በላይ ድጋፍ ሰጪ መሳሪያዎችንም እንደማይጠቀሙ በጥናቱ ውጤት ያሳያል። እንዲሁም መምህራኑ ለሰዋስው ትምህርት ያላቸው አመለካከት ዘመናዊነት የጎደለው ሲሆን ተማሪዎቹም የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ለመማር ያላቸው ፍላጎት መካከለኛ እና በመማርና ማስተማሩ ሂደት ላይም ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል ።

ህልፊት (2004) ‹‹የሰዋስው ይዘቶች በማስተማር የአሳተፊ የማስተማር ዘዴ አተገባበር ፍተሸ ፤በመቀሌ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች( በተመረጡ ዘጠነኛ ክፍሎች ናሙናነት››) በሚል ርዕስ ጥናት ያደረገች ሲሆን በጥናቱ የተገኘ ውጤት በሁለቱ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አሳታፊ የማስተማር ዘዴ አዘውትረው ይጠቀማሉ ይኸውም መምህራኑ የቡድን ውይይት ጥያቄና መልስ እና የክፍል ስራ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በተደጋጋሚ ይሰጣሉ በማለት ትገልፃለች ። ከዚህም በተጨማሪ መምህራኑ በመማር ማስተማር ሂደት የዕለቱን ትምህርት ርዕስ ማስተዋወቅ ፤ቅድመ ትምህርት ጥያቄዎችን በማቅረብ ፤ተማሪዎችን በማበረታታት

ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ ይሁን እንጂ መምህራን የዕለቱን ትምህርት አላማ አለማስተዋወቅ እያንዳንዱ የቡድን አባል በስራው ላይ ያለውን  ድርሻ አለማሳወቅ ተማሪዎችን ብቻ መስራት የማይሳተፍ ተማሪዎች እንዲሞክሩ አለማድረግ መምህራን ዘዴውን በተመለከተ ስልጠና አለመውሰድ የተማሪዎችን መብዛት ትልቅ ችግር ሊሆን መቻሉን በጥናቷ አረጋግጣለች  ።

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት የጥናት ስራዎች በሰዋስው ትምህርት አተገባበር ላይ የተጠኑ መሆናቸው ከዚህ ጥናት ጋር ሲያመሳስላቸው ፣ጥናቶቹ ከተማሪዎች ቋንቋ ዳራ አንፃር ያለውን ውጤታማነት ስላልዳሰሱ ይህንን ክፍተት ለመሙላት የተካሄደ ጥናት በመሆኑጥናቱን አዲስና ልዩ ያደርገዋል ። በተጨማሪም በቦታ ፣በክፍል ደረጃ ፣በፈተና ከጥናቶቹ ልዩነት አሳይቷል ።

## ምዕራፍ ሶስት
## የአጠናን  ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በህዳሴ ፍሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል የሰዋስው ትምህርት አተገባበ ውጤታማነት ከተማሪዎች ቋንቋ ዳራ አንፃር መፈተሽ ነው። አላማውን ከግብ ለማድረስ የጥናቱ የመረጃ ምንጮች እነማን እንደሆኑ ፣የጥናቱን  መረጃ ለመሰብሰብ ምን ምን ዘዴዎች በእንዴት አይነት መንገድ እንደተመረጡ እና ተግባራዊ እንደተደረጉ የሚያሳየው ዝርዝር መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል ።

### 3.1 የጥናቱ ዘዴ

ለዚህ ጥናት ለመረጃ ምንጭነት የሚያስፈልጉት የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና ተማሪዎች ለመረጃ ምንጭነት ይዉላሉ ።  የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው በሰነድ ፍተሸ ፣የጽሁፍ መጥይቅ፣በክፍል ምልከታ በፈተና በአላማ ተኮር የአመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል  ።  በመረጃ መሰብስቢያ ዘዴ የተሰበሰቡት መረጃዎች አይነታዊ ፣መጠናዊ የምርምር ዘዴ በመጠቀም በገለፃ ስልት የሚተነተኑ ይሆናሉ ።

### 3.2 የጥናቱ መረጃ ምንጮች

ለጥናቱ ዋና የመረጃ ምንጮች የ10ኛ ከፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና ተማሪዎች ናቸው ። በሰነድ ፍተሻ ፣ ለተማሪዎች የተዘጋጁ የጽሁፍ መጠይቆች ፣የክፍል ምልከታ ፣ ፈተና በአጋዥ የመረጃ ምንጭነት ያገለግላሉ ።

### 3.3  የናሙና አመራረጥ

#### 3.3.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን በወልቂጤ ከተማ መስተዳድር የሚገኙት አራት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሉ ። ጥናቱ ከአራቱ በአንዱ ትምህርት ቤት ላይ ትኩረት ያደርጋል  የህዳሴ ፍሬ ትምህርት ቤት ላይ ትኩረት ታደርጋለች  ። ትምህርት ቤቱ ተለይቶ የተመረጠበት ዋና ምክንያት በተለያዩ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ከአጎራባች ቀበሌዎች በመምጣት የሚማሩበት በመሆኑ ነው።እንዲሁም የቦታ ቅርበትን የተመደበላትን በጀት ከግምት በማስገባት በመሆኑም በአላማ ናሙና ስልት ተመርጧል ።

#### 3.3.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጡ የክፍል ደረጃ 10ኛ ክፍል ነው ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ካሉት የክፍል ደረጃዎች 10ኛ ክፍልን በአመች  ናሙና ስልት  የተመረጠ ሲሆን የተመረጠበት ምክንያት የጥናቱ አቅራቢ የምታስተምርበት የክፍል ደረጃ በመሆኑ ነው ።

#### 3.3.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በተተኳሪው ትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሁሉም ተመርጠዋል ። የተመረጡበት ምክንያት ተማሪዎቹን በቅርብ የሚያውቋቸው እና የሚያስተምሯቸው በመሆኑ አስተማማኝ መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ በመታመኑ ነው።

በናሙናነት በተመረጠው ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩና ለጥናቱ የተመረጡ መምህራን አጠቃላይ ዳራ

ሰንጠረዥ፡- 1 ከመምህራን  ዳራ

| የትምህርት ቤቱ ስም | የመምህራን ብዛት | | | የመምህራን የትምህርት ደረጃ | | የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ዲፕሎማ | ዲግሪ | |
| | | 3 | 3 | | 3 | 10ኛ ክፍል |

### 3.3.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በተተኳሪው ትምህርት ቤት ከሚገኙ 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ለመረጃ ሽጭነት በወሳኝ ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል ፡፡ የሚመረጡበት ምክኒያት ተማሪዎች በተለያየ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የተሻለ መረጃ ይሰጣሉ በሚል እሳቤ ነው፡፡

### 3.4  የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለዚህ ጥናት ተገቢ የሆኑትን መረጃ ለመሰብሰብ አጥኚዋ አራት ዓይነት  የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅማለች ፡፡ እነሱም ሰነድ ፍተሻ ፣የጽሁፍ መጠይቅ ፣የክፍል ምልከታና ፈተና ናቸው፡፡ በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በመገልገል የመረጃዎቹ አሰባሰብ በሚከተሉት ዘዴዎች ተከናውነዋል ፡፡

### 3.4.1 የሰነድ ፍተሻ

የጥናቱ ተተኳሪ በሆነው ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያዘጋጇቸውን የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ሳምንታዊ የትምህርት እቅዶች ከሶስት መምህራን ከእያንዳዳቸው አምስት አምስት ዕቅዶችን በመመርመር ሳምንታዊ የትምህርት ዝግጅቱ ከሰዋስው ትምህርት ዝግጅት አንፃር ስለመዘጋጀቱ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ እንዲሁም የተሰበሰበው መረጃ በአግባቡ በማደራጀት እና ከሰዋስው ትምህርት ዝግጅት ንድፈ ሀሳብ ጋር በማሰናሰል ትንተናው ተካሄዷል ፡፡

### 3.4.2 የፅሁፍ መጠይቅ

በፅሁፍ መጠይቅ መረጃ የተሰበሰበው በናሙናነት በተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ የጥናቱ ተተኳሪ ከሆኑት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከሚያስተምሯቸው የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል ነው፡፡የፅሁፍ መጠይቁ የሰዋስው ትምህርት አተገባባር ውጤታማነት ከቋንቋ ዳራ አንፃር በሚመለከት ተማሪዎች መረጃ ይሰጡ ዘንድ አስር ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ መረጃዎቹ  ስለመመምህራኑ የሰዋስው ትምህርት አተገባበር ፣የሚቀርበው የሰዋስው ህግጋት ካላቸው እውቀት ጋር ስላላው ተጣጥሞሽ ፤ሰዋስውንለመማር ስላላቸው ፍላጎት እና የመምህሩን ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ የሚዳስሱ ናቸው ፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች የተለያዩ የመስኩ ምሁራና ስለ ሰዋስው ትምህረት አተገባበር ከሚያቀምጡት ንድፈ ሀሳብ አንፃር የተዘጋጁ ሲሆን ተግባር ላይ ከመዋላቸው በፊት በአማካሪ መምህር አስተያየት ተስጥቶባቸዋል ፡፡

በአጠቃላይ ካሉት 10ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል ከ480ዎቹ ውስጥ 120 ተማሪዎችን በብድግ ብድጎሽ (Randm Sampling ) የናሙና ስልት አማካኝነት በመምረጥ የፅሁፍ መጠይቁን በጥንቃቄ እንዲሞሉት ከተረጡት ተማሪዎች መካከል 6ቱ መጠይቁን ሞልተው ያልመለሱ ሲሆን 4ቱ ደግሞ በትክክል ያልሞሉ በመሆኑ 10 ተማሪዎች ከጥናቱ ውጭ እንዲሆኑ በማድረግ ከ110 ተማሪዎች በተገኘ መረጃ ላይ በመመስረት ትንተና ተካሄዷል ።

### 3.4.3 የክፍል ውስጥ ምልከታ

የክፍል ምልከታ መረጃ ሰብሳቢው ሰው ምረጃ ለመሰብሰብ ከሚፈልግባቸው ተጠኚዎች አካባቢ በመሆን የሚያደርጉትንና የሚናገሩትን ነገር በቅርበት ሆኖ እያየና እየሰማ መረጃ የሚሰበስብበት ነው (ያለው 2001)። በመሆኑም የዚህን ምልክታ አለማ ለማሳካት መከታተያ ቅፅ (check list ) ተዘጋጅቶ ተግባር ላይ ውሏል ለምልከታው የተዘጋጀው መከታተያ ቅፅ ተግባር ላይ ከመዋሉ በፊት በአማካሪ መምህር አስተያየት ተሰጥቶበታል። በሌላ በኩል ቅፁ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን በመጀመሪያው ክፍል የትምህርት ቤቱን ስም የምልከታውን ቀንና ሰአት ፣ክፍልና ሴክሽን የተመዘገበበት ነው ።

ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የሰዋስው ትምህርት አተገባበር ሂደትን በሚመለከት ዝርዝር ነጥቦችን የያዘው የምልከታ ቅፁን መሰረት በማድረግ ለናሙና በተመረጡ 3 ክፍሎች ፣በእያንዳንዱ ሁለት ሁለት ክፍለ ጊዜያት በድምሩ ስድስት ክፍለ ጊዜያት በመግባት ምልከታ ተካሄዷል ። በምልከታዎቹ ሂደት የመማር ማስተማሩን ክንዋኔዎች በትኩረት በመከታተል መረጃዎች ተመዝግበው ተይዘዋል ።

### 3.4.4 ፈተና

ፈተናው እንዲመዝን የተፈለገው የሰዋስው ትምህርት አተገባባር ከቋንቋ ዳራ አንፃር ተማሪዎቹ ያላቸውን የችሎታ ደረጃ ተመጣጣኝ መሆን አለመሆኑም ለመፈተሽ ሲባል ነው ። ፈተናው ለተማሪዎቹ ከመቅረቡ በፊት  በአማካሪ መምህር እንዲገመገም  ከተደረገ በኂላ ማሻሻያ ተደርጎለት ወደ ስራ ተገብቷል ። በመሆኑም ፈተናው 100 ነጥብ የያዙ ሰዋሰዋዊ እዉቀትን የሚመዝኑ ጥያቄዎችን ይዟል ። የፈተና አስተራረሙን አስተማማኝ ለማድረግ ፈተናው በጥናቱ ምንም አይነት ተሳትፎ በሌላቸው የአማርኛ ቋንቋ የመጀመሪያ ድግሪ ባላቸው ሶስት መምህራን ታርሟል። ለጥናቱ ትንተና አመቺ ይሆን ዘንድ ካሉት 10ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል ከቋንቋ ዳራ አንፃር በጉራግኛ ፣አማርኛ ፣ኦርምኛ እና ከምባትኛ በእነዚህ አራት ቋንቋዎች አፋቸውን ከፈቱ ተማሪዎች መካከል  ስማኒያዎቹ በብድግ ብድጎሽ (Randam Sampling ) የናሙና ስልት አማካኝነት በመምረጥ ፈተናዉን እንዲፈተኑ በማድርግ ትንተናው ተካሄዷል ።

## ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተና

በዚህ የመረጃ ትንተና ክፍል የጥናቱ ተተኳሪ ከሆነው የህዳሴ ፍሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አተገባባር ከቋንቋ ዳራ አንፃር የሚመለከት በክፍል ውስጥ በተካሄዱ ምልከታዎች፣ በሰነድ ፍታሻ፣በጹሁፍ መጠይቅና በፌተና አማካኝነት የተገኙ መረጃዎች ትንተና ተካሄዶባቸዋል፡፡ እነዚህ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተገኙት መረጃዎች በምዕራፍ 2 ስር ከቀረቡት የሰዋስው ትምህርት አተገባባር ንድፈ ሀሳቦች አንፃር የተተነተኑ ናቸው ፡፡ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በማጣመር ትንተና ተደርጎባቸዋል ፡፡

### 4.1 ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

*የመምህራን የትምህርት ዝግጅት*

ማንኛውም አይነት ትምህርት የሰዋስውን ትምህርት ጨምሮ ለተማሪዎች እንዲቀርብ ሲታሰብ ቀዳሚው የመምህሩ ተግባር ትምህርቱን ማቀድ እንደሆነ በዚህ የጥናት ተዛማጅ ፅሁፍ ክፍል ስር የቀረበ የመስኩ ተማሪዎች ትወራዊ እሳቤ ይጠቁማል ፡፡ከዚህ አኳያ

❖ መምህርት አንድ በአምስቱም ሳምንታዊ የተምህርት ዝግጂት የጠቀሷቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ፣የትምህርቱ ይዘቶች አላማዎች በግልፅ የተወሰኑባቸው ሁለት ሁለት ዝርዝር አላማዎች ፣የማስተማሪያ መሳሪያዎች እንዲሁም በመምህሩና በተማሪዎች የሚከናወኑ ተግባራት የተገለፁበት ሳምንታዊ የትምህርት ዝግጅት ሲሆን መምህርቷ ባዘጋጁት የትምህርት እቅድ ውስጥ የተገለጹት የትምህርት ይዘቶችም ሆኑ ዝርዝር አላማዎች በመምህሩ መምሪያ ውስጥ ሰፍረው የሚገኙ ናቸው ፡፡ ይሁን እንጂ ዝርዝር አላማዎቹ ከስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው መርህ አንፃር ሲታዩ የትምህርቱን አጠቃላይ አላማ በተሟላ መልኩ ለማሳካት የሚያስችሉ ሁነው የሚገኙ አይደሉም ፡፡ ይኸውም አላማዎቹ በሰዋስዋዊ ትክክለኛነት ላይ እንጂ ተማሪዎች በትኩረት ልምምድ ደረጃ የሚቀርብላቸውን የመዋቅር ትምህርት ተግባቦታዊ ተግባራት እያከናወኑ መዋቅሮችን ኢ-ርቱዕ በሆነ መንገድ እንዲሰርጽ በሚያስችላቸው መልኩ የተነደፉ ሆነው አይታዩም ፡፡

❖ መምህርት ሁለት ሳምንታዊ የትምህርት ዝግጅት

ከመምህርቷ የተሰበሰበው አምስት ተከታታይነት ያላቸው ሳምንታዊ የትምህር እቅዶች ተመሳሳይነት የሚታይባቸው ሲሆን ለተማሪዎቻቸው ያዘጋጇቸው የትምህር ይዘቶች ፣ዝርዝር የትምህርት አላማዎች ፣በመምህሩና በተማሪዎቹ መከናወን የሚገባቸው ተግባራትና ለተምህርቱ ተግባራት ማከናወኛ የሚሆን የማስተማሪያ መሳሪያዎች በዝርዝር ተግልጸዋል፡፡

በትምህረት ዝግጅታቸው ላይ መምህርቷ የጠቀሷቸው የማስተማሪያ መሳሪያዎች የተማሪዎች መማሪያ መጻሐፍ ፣የመምህሩ መምሪያና" ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ " የተሰኘው በጌታሁን አማረ የተዘጋጀው የሰዋስው መጽሐፍ ናቸው ፡፡ መምህርቷ በትምህርት ዝግጅታቸው ዉስጥ የጠቀሷቸው በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የተገለጹት ሁለት ዝርዝር አላማዎች ከስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው የትምህርት አቀራረብ ጋር የሚጣጣሙ ሆነው ተገኝተዋል ፡፡

በሌላ በኩል ግን በመምህርቷ የትምህርት  ዝግጅት ውስጥ የተገለፁት ከላይ የተጠቀሱት የማስተማሪያ መሳሪያዎች መምህርቷ ትምህርቱን በግልጽ እንዲቀርቡና ተማሪዎቹም የቀረበላቸውን የሰዋስው ይዘቶች በ ትኩረት ልምምድ  ደረጃ እንዲለማመዱ ከመረዳት አልፈው ሰዋስዋዊ መዋቅሮቹን በተግባቦታዊ ልምምድ ደረጃ እንዲያሰርጹ ከማስቻል አኳያ ተገቢባለመሆናቸው የመምህሩ የትምህርት ዝግጅት ከዚህ አንፃር የተሟላ ሆኖ አልተገኘም

❖ የመምህር ሶስት ሳምንታዊ የትምህርት ዝግጅት

መምህርት ሶስት እንደ መምህርት አንድና ሁለት ሁሉ ያዘጋጁት የትምህርት እቅድ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ፣የትምህርቱ አላማዎች ፣ በመምህሩና በተማሪዎቹ መከናወን የሚገባቸው ተግባራትና በትምህርቱ ሂደት ውስጥም አገልግሎት ላይ የሚዉሉ የማስተማሪያ መሳሪያዎች መገለፃቸው ከስነ-ትምህርት ዝግጅታቸው ውስጥ የገለጿቸው ጉዳዮች በመምህርት አንድና በመምህርት ሁለት የትምህርት ዝግጅቶች ውስጥ ከተገለጹት ጋር ተመሳሳይነት የሚታይበት ሆኖ ተገኝቷል ፡፡

በርቱዕ  የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ላይ ብቻ ተመስርቶ የተዘጋጀው የመምህርት ሶስት የትምህርት እቅድ ኢ-ርቱዕ የትምህርት አቀራረብና ከዚሁ ጋር ሊታዩ የሚገባቸው ሌሎች ጉዳዮች ያልተገለጹበት ሆኖ መገኘት ዝግጅቱ የተሟላ አለመሆኑን የሚያመላክቱ ናቸው

በአጠቃላይ የሰነድ ፍተሻው የሚያመላክተው ከመምህራን የተሰበሰው ሳምንታዊ የትምህት እቅድ ከሰዋስው ትምህርት ዝግጅት አኳያ የተሟላ ሆኖ አለመገኘቱን ነው ፡፡

## 4.2 ለተማሪዎች ከቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ለናሙናነት ለተመረጡ 120 ተጠኚዎች የተዘጋጀው መጠይቅ ለተጠኚዎቹ ተሰራጭቶ 6ቱ መጠይቁን ሞልተው ያልመለሱ ሲሆን  4ቱ ደግሞ በትክክል አልሞሉም፡፡ በዚህ ምክንያት 10 ተጠኚዎች ከጥናቱ ውጭ እንዲሆኑ ተደርጎ ከ110 ተማሪዎች በተገኙ መረጃዎች ላይ በመመስረት ትንተናው እንዲካሄድ ተደርጓል ፡፡

ለተጠኚ ተማሪዎች የተሰጠው መጠይቅ የተማሪዎቹን ዳራዊ ሁኔታ ጠቋሚ መረጃዎችን ለማግኘት 2 ጥያቄዎችን ፣ እንዲሁም ተማሪዎቹ ለሰዋስው ትምህርት ያላቸውን ግንዛቤና ባለባቸው ክፍሎች ውስጥ የሰዋስው አተግባበር ገፅታን በሚመለከት ከተማሪዎቹ መረጃ ለመሰብሰብ  የቀረቡ 10 ዝግ ጥያቄዎች አጠቃሎ የያዘ ነው ፡፡

በነዚህ ጥያቄዎች አማካኝነት የተሰበሰቡ መረጃዎችም  ለዚህ ጥናት በዋናነት አገልግሎት ላይ ለዋለው የክፍል ምልከታ መረጃ  ደጋፊ በመሆን ያገለግላሉ፡፡

### 4.2.1 ዳራዊ ሁኔታ

ዳራዊ ሁኔታ ለዚህ ጥናት በናሙናነት የተመረጡ ተማሪዎችን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ፣ ተማሪዎች ከክፍል ዉጭ አብዛኛውን ጊዜ የሚገለገሉበትን ቋንቋ የሚጠቀምና በተለያዩ የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎች ለተሰበሰቡ መረጃዎች ደጋፊ የሚሆኑ ናቸው፡፡ እነዚህንም መረጃዎች ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ በማሳየት በመረጃዎቹ ላይ ትንተና ለማድርግ ተሞክሯል ፡፡

**ሰንጠረዥ፦ 2 የተማሪዎች ዳራ**

| የአፍ መፍቻ ቋንቋህ/ሽ | | | | | | | | ከክፍል ውጭ አብዛኛውን ጊዜ የምትግባባበት /ቢበት ቋንቋ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጉራጊኛ | | አማርኛ | | ኦሮምኛ | | ከምባትኛ | | ጉራግኛ | | አማርኛ | | | |
| ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | | |
| 42 | 38.18 | 38 | 34.54 | 20 | 18.18 | 10 | 9.09 | 20 | 18.18 | 90 | 81.81 | | |

የተማሪዎቹን ዳራዊ መረጃ ለማግኘት በመጠይቁ ዉስጥ ለቀረቡት ከላይ ለተጠቀሱት ሁለት ጥያቄዎች ከተማሪዎቹ የተሰጠው ምላሽ እንደሚያመላክት የጥናቱ ተተኳሪ በሆናው ክፍል ውስጥ ትምህርታቸዉን በመከታተል ላይ የሚገኙ ናሙና ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጉራግኛ ፣ አማርኛ ፣ኦሮምኛ እና ከምባትኛ ናቸው

በእነዚህ አራት ቋንቋዎች አፋቸዉን የፈቱ ተማሪዎች ብዛት በቋንቋዉ ተለይቶ ሲታይ 42 (38.18%) ተማሪዎች በጉራግኛ 38 (34.54% ) ተማሪዎች በአማርኛ 20 ( 18.18%) ተማሪዎች በኦሮምኛ 10 (9.09 %) ተማሪዎች በከምባትኛ አፋቸዉን የፈቱ ናቸው ።ይህም የሚያሳየው ጥናቱ ከተካሄደባቸው ተማሪዎች ዉስጥ በጣም ከፍተኛ ቁጥር ይዘው የሚገኙት አፋቸውን በጉራጊኛ የፈቱ ተማሪዎች መሆናቸውን ነው ።

ከዚህ ጥያቄ ጋር በተያያዘ እነዚህ ተማሪዎች ከክፍል ዉጭ ለአማርኛ ቋንቋ የመጋለጥ ሁኔታቸው ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ለቀረበላቸው ጥያቄ 90 (81.81%) ተማሪዎች ከክፍል ዉጭ ለሚያደርጉት ማህበራዊ መስተጋብር አብዛኛውን ጊዜ በአማርኛ እንደሚገለገሉ በሰንጠረዥ ላይ የተገለጸው የተማሪዎች ምላሽ ያመለክታል በሌላ በኩል ከክፍል ዉጭ ለሚያደርጉት ማህበራዊ ተራክቦ ጉራጊኛን የሚገለገሉ 20 (18.18 %) ተማሪዎች ብቻ መሆኑን ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ ያሳያል ።

### 4.2.2 በሰዋሰው ትምህርት ዓላማ ላይ የተማሪዎቹ ግንዛቤ

የተማሪዎቹን የሰዋሰው ትምህርት ዓላማ ግንዛቤ በሚመለከትና ሌሎች ከተማሪዎች ለተሰበሰቡ መረጃዎች የተዘጋጁት ዝግ ጥያቄዎች አምስት አማራጭ መልሶችን የያዙ ናቸው ።አማራጭ መልሶችም በጣም ከፍተኛ ፣ ከፍተኛ ፣ መካከለኛ ፣ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ የሚሉ ናቸው ። በእነዚህ አምስት ክፍሎች የተከፈሉ ምላሾች ብዛትም በእያንዳንዱ ክፍል ስር ተለይቶ ና በመቶኛ % ተሰልቶ ሰንጠረዥ ውስጥ እንዲሰፍር ተደርገዋል ።

ሰንጠረዥ ፡-3 በሰዋሰው ትምህርት ዓላማ ላይ የተማሪዎቹ ግንዛቤ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | የሰዋስው ትምህርት ዓላማ ከሌሎች የቋንቋ ኪሂሎች ጋር ተያያዥነት አለዉ | 25 | 22.72 | 10 | 9.09 | 30 | 27.27 | 45 | 40.90 | | |
| 2 | መምህርህ/ሽ ሰዋስውን ለምን እንደምትማር አዘውትረዉ ይገልጻሉ? | 20 | 18.18 | 15 | 13.63 | 20 | 18.18 | 55 | 50 | | |

የሰዋስው ትምህርት ዓላማ ከሌሎች የቋንቋ ኪሂሎች ትምህርት ዓላማ ጋር ስላለው ተያያዥነት ተማሪዎች ያላቸው ግንዛቤ በሚመለከት መረጃ ለማግኘት ለቀረበላቸው ጥያቄ 25 (22.72%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ ፣10 (9.09%) ተማሪዎች ከፍተኛ ፣30 (27.27%)ተማሪዎች ደግም መካከለኛ ብለው ሲመልሱ ቀሪዎች 45 (40.90%) ዝቅተኛ በማለት ምላሽ መስጠታቸውን በሰንጠረዥ ውስጥ ያለው አሃዝ ያመላክታል ፡፡ ይህ ደግሞ የሚያሳየው የሰዋስው ትምህርት ዓላማ ከሌሎች የቋንቋ ኪሂሎች ጋር ያለው ተያያዥነት ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

ከዚህ ጥያቄ ጋር በተያያዘ መምህራኑ ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርትን ለምን እንደደሚማሩ አዘዉትረዉ ሊገልጹላቸው እንደሆን ለቀረበላቸው ጥያቄ 20 (18.18%) ጊዜ በጣም ከፍተኛ ፣15 (13.63 %) ጊዜ ከፍተኛ ፣20 (18.18%) ጊዜ ደግሞ መካከለኛ ብለዉ የመለሱ ሲሆን ቀሪዎቹ 55 (50%) ተማሪዎች ደግሞ ዝቅተኛ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል ፡፡

ተማሪዎቹ ለሰዋስው ትምህርት ዓላማ ያላቸው የግንዛቤ ደረጃ ለማወቅ ከቀረበላቸው ሁለት ጥያቄዎች የሰጧቸው ምላሾች ተተቃለው ሲታዩ በጣም ከፍተኛው ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ስለትምህርቱ ዓላማ በቂ ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑን የሚያመለክቱ ሆነው ተገኝተዋል ፡፡

### 4.2 .3 የተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት ፍላጎት

ሰዋስውን ጨምሮ ለማንኛውም አይነት ትምህርት ዉጤታማነት የተማሪዎች ፍላጎት አዎንታዊ መሆን ወሳኝነት እንዳለው በዚህ ጥናት የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ክፍል ስር የተጠቀሰው የመስኩ ተመራማሪዎች ጥናታዊ መረጃ ይጠቁማል ፡፡ ከዚህ በመነሳት የተጠኚ ተማሪዎችን ፍላጎት ለማወቅ ከቀረበላቸው ጥያቄ የተገኘው መረጃ ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ ሰፍሮ ይገኛል ፡፡

**በሰንጠረዥ፡-4 ተማሪዎቹ ሰዋስውን ትምህርት ለመማር ያላቸው ፍላጎት**

| ተ. ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 3 | የሰዋስው ትምህርት ለመማር ፍለጎት አለህ /ሽ | 22 | 20 | 18 | 16.36 | 10 | 9.09 | 60 | 54.54 | | |

በሰንጠረዡ ውስጥ እንደሚታየው የአማርኛ ሰዋስውን ለመማር ያላቸው ፍላጎት በሚመለከት ለቀረበላቸው ጥያቄ 22 (20%) በጣም ከፍተኛ ፣18 (16.36%) ከፍተኛ 10 (9.09%) መካከለኛ ፣ 60 (54.54 ) ዝቅተኛ በማለት መልሰ ሰጥተዋል ይህ ደግሞ የሚያሳየው ተማሪዎቹን ሰዋስውን ለመማር ፍላጎት እንደሌላቸው የሚያሳይ ነው፡፡

### 4.2.4 እርማት /ምጋቤ ምላሽ/

በሰዋስው ትምህርት ውስጥ ከመምራኑ የሚሰጥ ምጋቤ ምለሽ ተማሪዎች እንዲያቁና እንዲያርሙ የሚረዳቸው መሆኑንና በትምህርቱ አቀራረብ ምጋቤ ምላሽ በልምመድ ሂደት ወይም ከልምምድ በኂላ ሊከናወን እንደሚገባ በዚህ ጥናት ምዕራፍ ሁለት ውስጥ የመስኩ ተመራማሪዎች ጥንታዊ መረጃ ያመለክታል ፡፡ ከዚህ ሀሳብ በመነሳት ለተጠኚ ተማሪዎች ጥያቄ ቀርቦላቸው ለጥያቄው የሰጡት ምላሽ ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ዉስጥ ሰፍሮ ይገኛል ፡፡

**ሰንጠረዥ፡-5 መምህራን ለክፍል ስራና ለቤት ስራ የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ የሰጡት ን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ጥያቄ | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 4 | የመምህራችሁ በክፍል ውስጥ በቤታችሁ እንድትሰሩ የሚሰጡአችሁን የሰዋስው መልመጃዎች አዘውትረው ያርማሉ | 45 | 40.90 | 28 | 25.45 | 20 | 18.18 | 17 | 15.45 | | |

ተማሪዎቹ ለቀረበላቸው ጥያቄ 45 (40.90%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ ፣28 (25.45%) ተማሪዎች ከፍትኛ ፣20 (18.18%) ተማሪዎች ደግም ዝቅተኛ ብለው ሲመልሱ ቀሪዎቹ ፣17 (15.45%) ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ መምህራን አዘውትረው እንደሚያርሙ ነዉ፡፡

ባጠቃላይ የተገኘው መረጃ እደሚያመላክትው መምህራኑ አዘዉትረው እንደሚያርሙ የሚያመለክት አውንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል ፡፡

**4.2.5 የፅህፈት ክሂል ልምምድ በተመለከተ**

የሰዋስው መዋቅር ትምህርት ከፅህፈት ክሂል ጋር ተቀናጅቶ መቅረብ ተማሪዎች ርቱዕ በሆነ መንገድ የሚቀርብላቸውን መዋቅር እንዲያጠናክሩ የሚረዳቸው በመሆኑም በሀረጎችና በዐ.ነሮች ደረጃ ላይ ብቻ ተወስነው የቋንቋዉን መዋቅር እንዲመስርቱ ማድረግ የሰዋስው ትምህርት ውጤታማ እንደሚያደርው በተዛማጅ ጽሁፍ ክፍል ተገልጿል ፡፡

ከዚህ በመነሳት ተጠኚ ተማሪዎች አጫጨር ድርሰቶች እንዲጽፉ የሚያበረታቱ መሆኑን ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ሰፍሮ ይገኛል ፡፡

ሰንጠረዥ ፡-6 የፅህፈት ክሂል  ልምምድ በተመለከተ በተመለከተ የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | መምህርህ/ሽ በክፍል ውስጥም ሆነ በቤት ስራ መልክ አጫጭር ድርሰቶችን እየፃፋችሁ ለክፍል ጓደኞታችሁ እንድታነቡ ያደርጋሉ ? | 30 | 27.27 | 35 | 31.81 | 20 | 18.18 | 25 | 22.72 | | |

የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራቸው በክፍል ውስጥም ሆነ በቤት ስራ መልክ አጫጭር ድርሰቶችን እየጻፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ እንድታነቡ ያደርጋሉ ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ 30 (27.27 %) በጣም ከፍተኛ ፣35 (31.81%) ከፍተኛ 20 (18.18%) መካከለኛ በማለት መልስ የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ ተማሪዎች ደግሞ 25 (22.72%)ዝቅተኛ  በማለት መልሰዋል ። ይህ የሚያመላክተው የአማርኛ ቋንቋ መምህራቸው በክፍል ዉስጥም ሆነ በቤት ስራ መልክ አጫጭር ድርሰቶችን እየጻፉ በክፍል ዉስጥ እንደሚያስነብቧቸው የሚያመለክት ነዉ።

## 4.2.6 መልመጃዎችን በተመለከተ

በመማሪያ መፅሀፋቸው ዉስጥ የቀረቡላቸው የሰዋስው መልመጃዎች ክብደት ወይም ቅለት በማስመልከት ለቀረቡላቸው ጥያቄ ተጠኚዎች የሰጡት ምላሽ ከዚህ በታች በሰንጠረዡ ሰፍሮ ይገኛል ።

**ሰንጠረዥ ፡-7 የመልመጃዎቹን ክብደትና ቅለት በተመለከተ ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 6 | በመመማሪያ መጽሐፍ /ሽ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች ከባድ ናቸው? | | | 40 | 36.36 | 36 | 32.72 | 34 | 30.90 | | |

የመማሪያ መጻሐፋቸው ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች ክብደትና ቅለት በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ 40 (36.36%) ከፍተኛ ሲሉ ፣36 (32፣72%) ተማሪዎች መካከለኛ በማለት የመለሱ ሲሆን ቀሪዎቹ 34 (30.40 %) ደግሞ ዝቅተኛ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

### 4.2.7 ተማሪዎች መምህራን ሰዋስውን በምን መልኩ እንደሚያስተምሩ የሰጡት ምለሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

**ሰንጠረዥ:-8 የሰዋስው ትምህርት ይዘቱ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ያለው ቅንጅት በተመለከተ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 7 | መምህራን ሰዋስውን የሚያስተምሩት ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ነው | 65 | 59.09 | 45 | 40.90. | | | | | | |

ከላይ እንደተጠቀሰው መምህራን ሰዋስውን የሚያስተምሩት ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት እንዲያስተምሩ ከተጠየቁት ተማሪዎች መካከል 65 (59.09%) ከፍተኛ በማለት ለሌሎች ክሂሎች ጋር በመቀናጀት እንደሚያስተምሩ ሲገልፁ 45 (40.90%) መካከለኛ በማለት ገልጸዋል ። ኪዘህ እንደምንረዳው ብዛት ያላቸው ተማሪዎች መምህራን የሰዋስው ትምህርት ሲያስተምሩ ከሌሎች ክሂሎችጋር በማጣመር እንደሚያስተምሩ ነው።

### 4.2.8 የመርጃ መሳሪያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ

ስለሰዋስው ትምህርት ውጤታማነት አስተዋጾ ከሚያደርጉ ነገሮች መካከል የመርጃ መሳሪያዎችን መጠቀም አንዱ እንደሆነ በጥናቱ ምዕራፍ ሁለት ስር የተገለጸ የመስኩ ተመራማሪዎች ጥናታዊ መረጃ ያመላክታል ። ከዚህ መርህ በመነሳት ለተጠኚዎቹ ከቀረበላቸው ጥያቄ የተገኘው ዉጤት በሰንጠረዡ ሰፍሮ ይገኛል ።

**ሰንጠረዥ :-9 የመምህራንን የድጋፍ ሰጪመሳሪያዎች አጠቃቀም የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 8 | በመምህርህ/ሽ የሰዋስው ትምህርት ሲያቀርቡላችሁ የትምህርት መረጃዎችን ይገለገላሉ | | | | | | | | | 110 | 100 |

የመምህራን የመረጃ መሳሪያዎችን መጠቀም ወይም አለመጠቀምን ለመፈተሽ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሁሉም ተጠኝዎች ማለትም 110 (100%)የሰጡት ምላሽ መምህራኑ የሰዋስውን ትምህርት ሲያቀርቡላቸው የትምህርት መረጃ መሳሪያዎችን እንደማይጠቀሙ ያመለክታል ።

### 4.2.9 የሚቀረበው ሰዋስዋዊ ይዘት ካለችሁ ዳራዊ እዉቀት ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ በሚመለከት ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

**ሰንጠረዝ ፡-10 የሰዋስው ይዘቱ ከተማሪዎች ዳራ ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 9 | መምህራችሁ የሚያቀርበው /ምታቀርበዉ ሰዋስዋዊ ይዘት ካላችሁ ዳራዊ እዉቀት ጋር ያለው ተጣጥሞሽ ምን ይመስላልለ? | 32 | 29.09 | 28 | 25.45 | 60 | 54.54 | | | | |

መምህራን የሚያቀርቡት ሰዋሰዋዊ ይዘቶች ካላችሁ ዳራዊ እዉቀት ጋር ያለዉ ተጣጥሞሽ ምን እንደሚመስል ከተጠየቁት ተማሪዎች መካከል 32 (29.09%) የሰጡት ምላሽ በጣም ከፍተኛ ፣28 (25.45%) ከፍተኛ ብለው ሲመልሱ ቀሪዎቹ 60 (54.54%) መካከለኛ ነው በማለት ምላሽ ሰጥተዋል ። ከዚህም እንደምንረዳው መምህራኑ የሚያቀርቡት ሰዋስዋዊ ይዘት ካላቸው ዳራዊ እውቀት ጋር ያለው ተጣጥሞሽ አጥጋቢ እንዳልሆነ ያመላክታል ።

#### 4.2.10 መምህራን ተማሪዎቹን የማበረታታቸውን መጠን በተመለከተ ተጠኚ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

**ሰንጠረዥ፡-11 መምህራን ተማሪዎችን የማበረታታቸውን መጠን በተመለከተ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | ጥያቄ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 10 | መምህራችሁ የሰዋስው ትምህትን ስትማሩ ትኩረታችሁን ትምህርቱ ላይ እንድታደርጉ ምን ያህል ያበረታቱችኋል | 44 | 40 | 28 | 25.45 | 25 | 22.72 | 13 | 11.81 | | |

ተማሪዎች መምህሮቻቸው በትምህርቱ ሂደት ላይ ተሳታፊ ይሆኑ ዘንድ ምን ያህል እንደሚያበረታቱ ተጠይቀዉ 44 (40%)ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣28 (25.45%)ከፍተኛ 25 (22.72%) መካከለኛ ብለዉ ሲመልሱ ቀሪዎቹ 13 (11.81%)ተማሪዎች ደግሞ ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል ከምላሽ የምንረዳው የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ተማሪዎቻቸውን የሚያበረታቱ መሆኑን ነው ።

በአጠቃላይ በተማሪዎችና በመምህራን መካከል ያለው ግኑኝነት መምህራን ተማሪዎቻቸውን የማበረታታቸው መጠን በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኙት ውጤቶች የሚያሰዩት መምህራኑ የሚያበረታታቸው መጠን ከፍተኛ እንደሆነ ነው።

### 4.3 ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ለናሙናነት በተመረጡት 3 ክፍሎች በእያንዳንዱ ክፍል ሁለት ሁለት ክፍለ ጊዜያት በድምሩ ስድስት ክፍል ጊዜያት በመግባት የመምህሩ የክፍል ዉስጥ የሰዋስዉ ትምህርት አተገባብር በመመልከት ትንተና ተደርጓል።

#### 4.3.1 የሰዋሰዉ ይዘቱን ለማቅረብ የተጠቀሙበትን አዉድ በተመለከተ

መምህራን የታላሚዉን ቋንቋ ሰዋሰዋዊ መዋቅር፣ ቅርፅና ፍቺን አጠቃቀም ለተማሪዎች በሚያቀረቡበት ወቅት አውዱን መጠቀም ይኖርባቸዋል። የታላሚዉን ቋንቋ ሰዋሰዋዊ መዋቅር በአውድ ማቅረብ ተማሪዎች የቋንቋውን ምንነትና አጠቃቀም እንዲገነዘቡ

ከማድረግም በላይ በትምህቱም ላይ እንዲመሰጡ በማድረግ ፍላጎታቸዉን ያነሳሳል። በተጨማሪም ጥሩ አውድ የተማሪዋች ዳራዊ እዉቀት ስለሚያገናዝብ የቀረበላቸውን አረፍተነገር ከመደጋገም ባሻገር የራሳቸዉን አረፍተነገር እንዲመሰርቱ በር ይከፍታል (Widdowson 1990 Cunnings Worth 1984 Harmer 1987)፡፡

መምህራን የሰዋሰዉ ይዘትን በአውድ ማቅረባቸዉንና የአውዱንም ተገቢነት በተመለከተ የተደረገዉ ምልከት የሚከተለውን ይመስላል፡፡

**ሠንጠረዥ፡-12 መምህራን የሰዋስውን ይዘቱን የተጠቀሙበት አውድ መጠን በተመለከተ የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የምልከታ ነጥብ | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 11 | የሰዋሰዉ ይዘቱን ለማቅረብ የተጠቀሙት አዉድ ተገቢነት | | | | | 2 | 33.33 | 3 | 50 | 1 | 16.66 |

መምህራን የሰዋስው ይዘትን ለማቅረብ የሚጠቀሙትን አውድ ተገቢነት በተመለከተ በተደረገው ተደጋጋሚ መልከታ መካከል 2 (33.33%) ጊዜ መካከለኛ 3 (50%) ጊዜ ዝቅተኛ እና1 (16.66) ጊዜ ደግሞ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ከዚህም የምንረዳው መምህራኑ የሰዋስው ይዘትን ለማቅረብ በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ አውዶችን የማይጠቀሙ መሆን ነው፡፡

### 4.3.2 ድጋፍ ሰጭ መሳሪያዎችን በተመለከተ

ተማሪዎች አንድን ትምህርት  በቀላሉ እንዲረዱና ከራሳቸው ጋር እንዲያዋህዱት የድጋፍ ሰጭ መሳሪያዎች ሚና ከፍተኛ ነው ፡፡ ይህንንም ለማድረግ መምህራን ደጋፊ የሆኑ እንደ ስዕል ፣ምንባብ ፣መርጃ መጽሀፍት ወዘተ… መጠቀም ይችላሉ (Cunning Swith 1984 ፣50)፡፡ በዚህ መሰረት በመማሪያ ክፍል ውስጥ የተደረገው ምልከታ የሚከተለውን ይመስላል ፡፡

**ሰንጠረዥ፡-13 የመምህራን የደጋፍ ሰጪ መሳሪያዎች አጠቃቀም በተመለከተ የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | የምልከታ ነጥብ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 12 | የድጋፍ ሰጭ መሳሪያዎች ምርጫና አተገባበር | | | | | | | 1 | 16.66 | 5 | 83.33 |

የመምህራን የድጋፍ ሰጭ መሳሪያዎች አጠቃቀም ልምድ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ አተገባበር ላይ አልታየም። ምክኒያቱም ከተደረገው ከስድስት ተደጋጋሚ ምልከታ መካከል 1 (16.66%) ጊዜ ዝቅተኛ እና 5 (83.33%) ጊዜ ደግሞ በጣም ዝቅተኛ ነው ፡፡ ከሶስቱ ተጠኚ መምህራን መካከል አንዷ መምህርት ብቻ ‹‹ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው ›› የሚል መጽሀፍ ይዘው መግባታቸው ተስተውሏል ፡፡

### 4.3.3 ሰዋስው ይዘቱን ከተማሪዎች ዳራ ጋር ያለው ተጣጥሞሽ

በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚቀርቡት ሰዋሰዋዊ ይዘቶች ፣ምሳሌዎች እና መልመጃዎች የተማሪውን ዳራ ያገናዘቡ መሆን አለባቸው ፡፡ ይኸውም ከተማሪው እድሜ ፣ የከፍል ደረጃ ከመጣበት ማህበረሰብ ጋር አብሮ የሚሄድ ከሆነ የተማሪውን ስሜት የመሳብ አቅሙ ከፍተኛ ነው ፡፡ (widdodo 2006) :: ይህንንም አስመልክቶ የተደረገው የክፍል ምልከታ የሚከተለውን ይመስላል ሰንጠረዥ

**ሰንጠረዥ ፦14 የሰዋስው ይዘቱ ከተማሪዎች ዳራ ጋር ያለውን ተጣጥሞሽ በተመለከተ የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | የምልከታ ነጥብ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 13 | ህግጋቱ ተማሪዎች ከዚህ በፊት ካላቸው ዳራ እውቀት ጋር ያላቸው ተጣጥሞሽ | | | | | 4 | 66.66 | 2 | 33.33 | | |

ከሰንጠረዡ እንደምንረዳው በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚቀርቡት የሰዋስው ይዘቶችና መልመጃዎች ከተማሪዎች ዳራ ጋር ያለው ተጣጥሞሽ 4 (66.66%) ጊዜ መካከለኛ እና 2 (33.33%) ጊዜ ደግም ዝቅተኛ ነው። ይህ የሚያመላክተው ከተማሪዎች የዕለት ከዕለት ህይወትና ከመጡበት ማህበረሰብ ጋር አብሮ የመሄድ ደረጃው ዝቅተኛ መሆኑን ያመላክታል።

### 4.3.4 ምጋቤ ምላሽን በተመለከተ

ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት በሚማሩበት ወቅት ለሚፈጽሙት ስህተት በተማሪው ወይም በመምህሩ አማካኝነት እርማት ሊሰጣቸው ይገባል ፡፡ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ደረጃ የተለያየ መሆን አለበት ፡፡ በልምምድ ደረጃ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ህግጋት ትክክለኛውን ቅርጽና ትርጉም ሊረዱ ዘንድ መምህሩ በሚፈጽሙት ስህተት ላይ ጣልቃ በመግባት እርማት መስጠት ይኖርበታል። በአፍልቆት ደረጃ ግን ተግባቦቱ መቋረጥ ስሌሌለበት ተማሪዎች የሚፈጽሙትን በማስታወሻ ላይ ጽፎ በመያዝ መጫረሻ ላይ መጋቤ ምላሽ መስጠት አለበት ፡፡ እርማቱ ሁሉንም ተማሪዎች ያማከለ መሆን ይኖርበታል (Harmer 1987፣ 41፣ ur 1988፣ celce murcia 1991፣229)::

ሰንጠረዥ፡-15 የመምህራናኑን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የምልከታ ነጥብ | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 14 | በልምምድ ደረጃ የመምህሩ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ | 2 | 33.33 | | | 4 | 66.66 | | | | |
| 15 | በአፍልቆት ደረጃ የመምህሩ የመጋቤ ምላሽ አሰጣጥ | 1 | 16.66 | | | 3 | 50 | 2 | 33.33 | | |
| 16 | መጋቤ ምላሹ ሁሉንም ተማሪዎች ማማከሉ | | | 2 | 33.33 | | | 2 | 50 | 1 | 16.66 |

በልምምድ ደረጃ የመምህሩ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ  በተመለከተ ስድስት ጊዜ ከተደረገው ምልከታ መካከል 2 (33.33%) ጊዜ በጣም ከፍተኛ ሲሆን ፣4 (66.66%) ጊዜ መካከለኛ እንደሆነ ያመላከተው፡፡ይህ ደግሞ የሚያመላክተው  በልምምድ ወቅት ተማሪዎች ለሚፈጽሙት ስህተት መምህራኑ በተወሰነ መልኩ እርማት የሚሰጡ መሆኑ ነው ፡፡

በተጨማሪ በአፍልቆት ደረጃ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ህግጋት በመጠቀም ተግባቦት በሚያከናውኑበት ወቅት ለሚፈጽሙት ስህተት መምህራኑ ተግባቦቱን በማቋረጥ ምጋቤ ምላሽ የሚሰጡበት ሁኔታ ለማጣራት በተደረገው ምልከታ 1 (16.66%) ጊዜ በጣም ከፍተኛ ፣3 (50%) ጊዜ መካከለኛ እና 2(33.33%) ጊዜ ደግሞ ዝቅተኛ ነው ፡፡ ይህ የሚያመላክተው መምህራኑ አንዳንዴ የተማሪዎችን ተግባቦት በማቋረጥ ምጋቤ ምለሽ የሚሰጡ መሆኑን ነው ፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎቹ ሀሳባቸውን በነፃነት እንዳይገልጹ ስለሚያደርግ መሻሻል ይኖርበታል ፡፡

መምህራኑ የሚሰጡት እርማት በተመለከተ ሁሉንም ተማሪዎች ያማከለ መሆኑን በተመለከተ ከተደረገው ምልከታ 2 (33.33%) ጊዜ ከፍተኛ ሲሆን ፣3 (50%) ጊዜ ዝቅተኛ እና 1 (16.66%) ጊዜ ደግሞ በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ታያቷል ፡፡ ከዚህ  የምንረዳው የመምህራኑ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ሁሉም ተማሪዎች የማያማክል መሆኑ ነው፡፡

መምህራኑ እርማት የሚሰጡት እጅ ለሚያነሱ ከፊት ለፊት ለተቀመጡት ተማሪዎች ብቻ ነበር ።

## 4.3.5 የተማሪዎች ተሳትፎ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

ሰንጠረዥ :-16 የተማሪዎች ተሳትፎ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የምልከታ ነጥብ | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 17 | ተማሪዎች በትምህርት ወቅት የነበራቸው ሚና | | | 2 | 33.33 | 3 | 50 | 1 | 16.66 | | |

ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የነበራቸው ሚና በተመለከተ 2 (33.33%) ጊዜ ከፍተኛ ሲሆን ፣3 (50%) ጊዜ መካከለኛ ሲሆን 1 (16.66%) ጊዜ ደግሞ ዝቅተኛ ነዉ ። ይህ ደግሞ የሚያመለክተው የተማሪዎች ተሳትፎ መካከለኛ መሆኑን ነው።

## 4.3.6 የቀረቡት ምሳሌዎችና መልመጃዎች ተግባቦትን ለማከናወን ያላቸው ሚና

መምህራን አዲስ የሰዋስው ይዘት በሚያስተምሩበት ወቅት ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው ህግጋት በቀላሉ መረዳት ይችሉ ዘንድ በቂ ምሳሌዎችን ማቅረብ ይኖርባቸዋል። መልመጃዎቹንም በተመለከተ ተማሪዎች ሙሉ አቅማቸውን ተጠቅመው በቋንቋው ተግባቦት እንዲያከናዉኑ የሚያስችሉ፣ በእውኑ አለም ያለውን የቋንቋ አጠቃቀም ያካተቱና የአመራማሪነት ባህሪ ያላቸውን መልመጃዎች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል (celece Murcia 1988 ፣ Ur 1988፣ Grant 1989 ፣15 ) ።

**ሰንጠረዥ ፡-17 መምህራን የሚያቀርቧቸውን ምሳሌዎችና ምልመጃዎች የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የምልከታ ነጥብ | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 8 | መምህሩ ያቀረባቸዉ ምሳሌች ብዛትና የመልመጃዎቹ ተማሪዎችን የማመራመር ደረጃና ተግባቦትን ለማከናወን ያለቸውን ሚና | | | | | 2 | 33.33 | 4 | 66.66 | | |

መምህራኑ ሰዋስውን በሚያቀርቡበት ወቅት የሚጠቀሙበትን ምሳሌዎች ብዛትና የመልመጃዎቹ የአመራማሪነት ደረጃና ተግባቦትን ለማከናወን ያላቸው ሚና በተመለከተ የተደረገው ምልከታ 2(33.33 %) ጊዜ መካከለኛ ፤4(66.66%) ጊዜ ደግሞ ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህ የሚያመላክተው የተወሰኑ መረጃዎች ብቻ በማቅረብ እንደሚያስተምሩ ተስተውሏል፡፡

### 4.3.7 ለልምድ የቀረቡትን ብልሃቶች በተመለከተ

የታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ መዋቅር ላይ ተማሪዎች ልምምድ ያደርጉ ዘንድ የተለያዩ ብልሀቶችን መጠቀም ይቻላል ከነዚህም መካከል ምልልስ ፤ ሚና ጨዋታ ፤ልምምድ ወዘተ... ናቸው ፡፡ እነዚህ ብልሀቶች ከሚቀርበው ሰዋሰዋዊ ይዘት፣ ከመልመጃዎችና ከተማሪዎች ደረጃ አንፃር የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ ፡፡ በመሆኑም መምህራን ከተማሪዎቹ ፤ለመልመጃዎቹና ከሰዋሰዋዊ ይዘቱ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ በማጤን መጠቀም ይኖርባቸዋል ፡፡ በተጨማሪም እነዚህን ብልሀቶች መጠቀም ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ በንቃት እንዲሳተፉና የታላሚዉን ቋንቋ ህግጋት በቀላሉ እንዲረዱ ያግዛሉ (Harmer 1977፣ Cunning Sworth 1984 ፤Ur 1988)

በመሆኑም የጥናቱም ተተኳሪ መምህራን የሰዋስው መዋቅርን ለማለማመድ የተጠቀሙትን ብልሃት ተገቢነት በተመለከተ የተደረገው የክፍል ውስጥ ምልከታ የሚከተለውን ይመስላል ፡፡

ለልምምድ የቀረቡ ብልሀቶች ተገቢነት የሚያሳይ ሰንጠረዠ

**ሰንጠረዥ፡-18 ለልምምድ የቀረቡ ብልሀቶች ተገቢነት የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የምልከታ ነጥብ | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 19 | ለልምምድ የቀረቡ ብልሃቶች ተገቢነት | | | 1 | 16.66 | 3 | 50 | 2 | 33.33 | | |

ሰንጠረዥ18 ፡- ከሰንጠረዡ የምንረዳው መምህራን ለልምምድ የሚጠቀሙት ብልሃቶችን ተገቢነት በተመለከተ ከተደረገው ስድስት ተደጋጋሚ መልከታ መካከል 1(16.66 %) ጊዜ ከፍተኛ ፣ 3 (50 %) ጊዜ መካከለኛ ፣2 ( 33.33 %) ጊዜ ዝቅተኛ መሆኑን ነው ፡፡ ይህም የሚያመላክተው መምህራን በታላሚው ቋንቋ ሰዋሰዋዊ መዋቅር ላይ ብልሃቶችን የሚጠቀሙበት አጋጣሚ መካከለኛ እንደሆነ ነው ፡፡

**4.3.8 በአፍልቆት ጊዜ የመምህሩን ጣልቃ ገብነት በተመለከተ**

የሰዋስው ይዘትን ክፍል ውስጥ ለማስተማር ከምንጠቀምባቸው አራት አይንት ደረጃዎች መካከል አንዱ የአፍልቆት ( production )ነው ፡፡ ተማሪዎች በዚህ ደረጃ የታላሚዉን ቋንቋ ሰዋስው ለተግባቦት የሚጠቀሙበት ወቅት በመሆኑ የመምህሩ ጣልቃ ገብነት በጣም ዝቅተኛ ሆኖ መገኘት አለበት ፡፡ በዚህም ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነፃነት የመግለፅ አድል ያገኛሉ (Cunning Sworth 1984 ) ፡፡ይህን በተመለከተ የተደረገው ምልከታ በሰንጠረዡ ላይ ሰፍሮ ይገኛል ፡፡

**ሰንጠረዥ ፡-19 መምህራኑ በአፍልቆት ጊዜ የሚያደርጉት ጣልቃ ገብነት ደረጃ የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የምልከታ ነጥብ | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 19 | በአፍልቆት ጊዜ የመምህሩ ጣልቃ ገብነት ደረጃ | | | | | 4 | 66.66 | 2 | 33.33 | | |

ሰንጠረዥ 19 :- እንደሚያመላክተው መምህራኑ በአፍልቆት ጊዜ የሚያደርጉት ጣልቃ ገብነት 4 (66.66 %) ጊዜ መካከለኛ ፣2 (33.33 %) ጊዜ ደግሞ ዝቅተኛ ሆኖ ታይቷል ። ከዚህ የምንረዳው የመምህራኑ ጣልቃ ገብነት መክከለኛ መሆኑ ነው ይህ ደግሞ ተማሪዎች ሃሳባቸውን በነፃነት እንዳይገልጹ የሚያደርግ ስለሆነ መሻሻል ይኖርበታል ።

## 4.4 የፈተና ውጤት ትንተና

በዚህ የመረጃ ክፍል የሰዋሰው ትምህርት አተገባበር ውጤታማነት ከቋንቋ ዳራ አንጻር በአማርኛ ቋንቋ አፈፊት ተማሪዎች እና ኢ-አፈፊት ተማሪዎች መካከል በሰዋስው ዕውቀት መመዘኛ ሁለት ፈተናዎች ያመጡት አማካኝ ውጤት ትንተና ከነማብራሪያው ከቀድሞ አጥኚዎች ግኝት አንጻር ይቀርባል።

### 4.4.1. የምርጫ ጥያቄዎች

**ሠንጠረዥ 20: የምርጫ ጥያቄዎች ውጤት ናሙና ቲ - ቴስት**

| የጥያቄው ዓይነት | የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ | ናሙና ተማሪዎች ብዛት | የፈተናው ዓይነት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የስህተት አማካይ | የነፃነት ደረጃ | የ t ዋጋ | የ p ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የምርጫ ጥያቄዎች | አማርኛ | 22 | ፈተና 1 | 9.23 | 1.901 | .405 | 42 | -.167 | .868 |
| | | 22 | ፈተና 2 | 9.32 | 1.701 | .363 | | | |
| | ጉራጊኛ | 28 | ፈተና 1 | 8.21 | 1.701 | .238 | 54 | -.214 | .832 |
| | | 28 | ፈተና 2 | 8.29 | 1.258 | .235 | | | |
| | ኦሮምኛ | 20 | ፈተና 1 | 8.25 | 1.243 | .260 | 38 | -1.097 | .280 |
| | | 20 | ፈተና 2 | 8.70 | 1.418 | .317 | | | |
| | ከንባትኛ | 10 | ፈተና 1 | 8.20 | 1.317 | .416 | 18 | -.387 | .703 |
| | | 10 | ፈተና 2 | 8.50 | 2.068 | .654 | | | |

ምንጭ የ SPSS ውጤት, 2023

ከላይ በሰንጠረዥ 20 እንደተጠቀሰው በአማርኛ፣ በጉራጊኛ፣ በኦርምኛ እና ከንባትኛ ቋንቋ አፈፊት ተማሪዎች ላይ የዉጤት ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማነጻጸር ቲ-ቴስት ዉጤት ተካሄዷል ። በዚህም መሠረት በተዘጋጁት የምርጫ ጥያቄዎች በሁለቱ መካከል ጉልህ

ልዩነት አልታየም፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት የእያንዳንዳቸው የቲ ዋጋ ከ -2.000 ስለሚበልጥ እንዲሁም የእያንዳንዳቸው የp ዋጋ ከ.05 በላይ በመሆኑ ነው ፡፡ በአራቱም የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች በፈተና 1 እና በፈተና 2 የምርጫ ጥያቄዎች መካከል የጎላ ልዩነት የለም ፡፡ ከዚህ ውጤት በመነሳት ለመረዳት የሚቻለው በተሰጣቸው ጥያቄዎች ላይ የተማሪዎች ውጤት ወጥ ነው ሊባል ያስችላል ፡፡

### 4.4.2. ቃላትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

**ሰንጠረዥ 21 : ቃላትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ውጤት ናሙና ቲ - ቴስት**

| የጥያቄው ዓይነት | የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ | ናሙና ተማሪዎች ብዛት | የፈተናው ዓይነት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የስህተት አማካይ | የነፃነት ደረጃ | የ t ዋጋ | የ p ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቃላትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች (5%) | አማርኛ | 22 | ፈተና 1 | 4.05 | .653 | .139 | 42 | -1.339 | .188 |
| | | 22 | ፈተና 2 | 4.27 | .456 | .097 | | | |
| | ጉራጊኛ | 28 | ፈተና 1 | 3.50 | .745 | .141 | 54 | -.541 | .591 |
| | | 28 | ፈተና 2 | 3.61 | .755 | .145 | | | |
| | ኦሮምኛ | 20 | ፈተና 1 | 3.55 | .686 | .153 | 38 | -1.086 | .284 |
| | | 20 | ፈተና 2 | 3.80 | .768 | .172 | | | |
| | ከንባትኛ | 10 | ፈተና 1 | 3.40 | .699 | .221 | 18 | -1.411 | .175 |
| | | 10 | ፈተና 2 | 3.90 | .876 | .277 | | | |

ምንጭ የ SPSS ውጤት, 2023

ከላይ በሰንጠረዥ 21 የሰፈሩት ስታቲስቲካዊ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት በጥያቄ ሁለት ቃላት የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎችን በተመለከተ በሁለቱም ፈተና መካከል ጉልህ ልዩነት አልታየም፡፡ ምክንያቱም የእያንዳንዳቸው የp ዋጋ ከ.05 በላይ ስለሆነ ነው ፡፡ የተማሪዎችን ውጤት በማየት በተሰጣቸው ጥያቄዎች አራቱም ቡድኖች ያመጡት ውጤት ወጥ ነው ሊባል ይችላል፡፡

### 4.4.3. ስረዓታቸውን የጠበቁ ሰዋሰዋዊ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት

**ሰንጠረዥ 22: ስረዓታቸውን የጠበቁ ሰዋሰዋዊ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት ውጤት ናሙና ቲ - ቴስት**

| የጥያቄው ዓይነት | የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ | ናሙና ተማሪዎች ብዛት | የፈተናው ዓይነት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የስህተት አማካይ | የነፃነት ደረጃ | የ t ዋጋ | የ p ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ስረዓታቸውን የጠበቁ ሰዋሰዋዊ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት ውጤት (10 %) | አማርኛ | 22 | ፈተና 1 | 7.18 | .853 | .182 | 42 | -2.790 | .010 |
| | | 22 | ፈተና 2 | 7.68 | .995 | .212 | | | |
| | ጉራጊኛ | 28 | ፈተና 1 | 6.86 | .932 | .176 | 54 | 14.176 | .000 |
| | | 28 | ፈተና 2 | 7.42 | .737 | .139 | | | |
| | ኦሮምኛ | 20 | ፈተና 1 | 6.75 | 1.118 | .250 | 38 | .147 | .884 |
| | | 20 | ፈተና 2 | 6.70 | 1.037 | .231 | | | |
| | ከንባትኛ | 10 | ፈተና 1 | 6.50 | 1.269 | .401 | 18 | -1.129 | .274 |
| | | 10 | ፈተና 2 | 7.10 | 1.101 | .348 | | | |

ምንጭ የ SPSS ውጤት, 2023

ከላይ ሰንጠረዥ 22 የሰፈሩት መረጃዎች እንደሚያመላክቱት በጥያቄ ሶስት የጥያቄ አይነት ስርዓታቸውን የጠበቁ ሰዋስዋዊ ዐ.ነገሮችን መመስረት የሚጠይቅ ነው፡፡ በዚህ የጥያቄ አይነት አራቱም ቡድኖች ማለት አማርኛ፣ጉራጊኛ፣ኦሮምኛ እና ከንባትኛ ቋንቋ አፈፊት ተማሪዎች ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያመላክታል ፡፡ በትንተናው ውጤት መሰረት አማርኛ እና ጉራጊኛ እያንዳንዳቸው በተናጠል በፈተና 1 እና ፈተና 2 መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ነው፡፡ ምክንያቱም የ p ዋጋቸው ከ .05 በታች ስለሆነ

ነው፡፡ ነገር ግን በኦሮምኛ እና በከንባትኛ መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩ ታይቷል ፡፡ ምክንያቱም የ p ዋጋቸው ከ .05 በላይ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ትንተና ውጤት መረዳት የሚቻለው የተማሪዎቹ ውጤት በአራቱ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች መካከል የውጤት መሻሻል ላይ ወጥነት አለመኖሩን ነው፡፡

### 4.4.4. የሐረጎችን መሪ ቃል እና የሐረጎችን ዓይነት መጻፍ

**ሰንጠረዥ 23: የሐረጎችን መሪ ቃል እና የሐረጎችን ዓይነት መጻፍ ዉጤት ናሙናዎች ቲ - ቴስት**

| የጥያቄው ዓይነት | የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ | ናሙና ተማሪዎች ብዛት | የፈተናው ዓይነት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የስህተት አማካይ | የነፃነት ደረጃ | የ t ዋጋ | የ p ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **የሐረጎችን መሪ ቃል እና የሐረጎችን ዓይነት መጻፍ ውጤት** (10%) | አማርኛ | 22 | ፈተና 1 | 7.05 | .990 | .232 | 42 | -3.358 | .002 |
| | | 22 | ፈተና 2 | 8.09 | .971 | .207 | | | |
| | ጉራጊኛ | 28 | ፈተና 1 | 6.32 | .772 | .146 | 54 | -5.484 | .000 |
| | | 28 | ፈተና 2 | 7.54 | .881 | .167 | | | |
| | ኦሮምኛ | 20 | ፈተና 1 | 5.95 | .945 | .211 | 38 | -3.474 | .001 |
| | | 20 | ፈተና 2 | 6.85 | .671 | .150 | | | |
| | ከንባትኛ | 10 | ፈተና 1 | 5.80 | .991 | .442 | 18 | -2.591 | .002 |
| | | 10 | ፈተና 2 | 6.30 | .687 | .512 | | | |

ምንጭ የ SPSS ውጤት, 2023

ከዚህ ሰንጠረዥ 23 የሰፈሩት መረጃዎች እንደሚያመላክቱት ጥያቄ አራት የሀረጎችን መሪቃልና የሀረጎችን አይነት መጻፍ የሚጠይቅ ነው፡፡ በትንታኔው ዉጤት መሰረት በአራቱም የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች የፈተና 1 እና ፈተና 2 ውጤት እንደሚያሳየው በመካከላቸው የጎላ ልዩነት እንዳላቸው በተደረገው ናሙና ቲ-ቴስት ዉጤት ተረጋግጧል፡፡ ምክንያቱም የእያንዳንዳቸው የp ዋጋ ከ .05 በታች ስለሆነ ነው፡፡ ከዚህ ትንተና ውጤት መረዳት የሚቻለው የሐረጎችን መሪ ቃል እና የሐረጎችን ዓይነት መጻፍ ጥያቄ ላይ ውጤቱ የተሻሻለ መሆኑን ነው ፡፡

### 4.4.5. እማሪያዊ እና ፍካሪያዊ ፍቺ መስጠት

**ሰንጠረዥ 24: እማሪያዊ እና ፍካሪያዊ ፍቺ የመስጠት ውጤት ናሙና ቲ - ቴስት**

| የጥያቄው ዓይነት | የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ | ናሙና ተማሪዎች ብዛት | የፈተናው ዓይነት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የስህተት አማካይ | የነፃነት ደረጃ | የ t ዋጋ | የ p ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| እማሪያዊ እና ፍካሪያዊ ፍቺ መስጠት (10%) | አማርኛ | 22 | ፈተና 1 | 8.09 | .971 | .207 | 42 | -2.833 | .004 |
| | | 22 | ፈተና 2 | 8.64 | .968 | .214 | | | |
| | ጉራጊኛ | 28 | ፈተና 1 | 7.18 | .945 | .179 | 54 | -2.807 | .007 |
| | | 28 | ፈተና 2 | 7.93 | .952 | .199 | | | |
| | ኦሮምኛ | 20 | ፈተና 1 | 6.65 | .933 | .209 | 38 | -5.728 | .000 |
| | | 20 | ፈተና 2 | 7.77 | .641 | .143 | | | |
| | ከንባትኛ | 10 | ፈተና 1 | 6.30 | .960 | .367 | 18 | -2.321 | .009 |
| | | 10 | ፈተና 2 | 7.10 | .924 | .482 | | | |

ምንጭ የ SPSS ውጤት, 2023

በታቀደው መሰረት በእማሪያዊ እና ፍካሪያዊ ፍቺ መስጠት ዙሪያ በተዘጋጀው ፈተና 1 እና ፈተና 2 ውጤት መሰረት በአራቱም የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች የጎላ ልዩነት እንዳላቸው የተደረገው የናሙና ቲ-ቴስት ውጤት አመላክቷል። ምክንያቱም የእያንዳንዳቸው የp ዋጋ ከ .05 በታች ስለሆኑ ነው። ከዚህ ትንተና ውጤት መረዳት የሚቻለው የተማሪዎቹ ውጤት መሻሻሉን ነው ።

### 4.4.6 የአማካይ ውጤቶች ንጽጽር

ከንዑስ 4.2.1.1 እስከ 4.2.1.5 በአፈፊት (አማርኛ) እና በኢ- አፈፊት (ጉራጊኛ፣ኦሮምኛ፣ እና ከንባትኛ) ቋንቋ አፈፊት ተማሪዎች በተዘጋጁ አምስት ዓይነት ጥያቄዎች በፈተና 1

እና በፈተና 2 መካከል የጎላ ልዩነት መኖር አለመኖሩን የተተነተነውን አይተናል ፡፡ ቢሆንም እንደ አጠቃላይ ልዩነት መኖር አለመኖሩን መመርመር አስፈላጊና የጥናቱንም ውጤት የበለጠ ስለሚያጠናክረው ከዚህ በመቀጠል ራሱን ችሎ የናሙና ቲ - ቴስትን በመጠቀም በፈተና 1 እና በፈተና 2 መካከል የጎላ ልዩነት መኖር አለመኖሩን እንመለከታለን፡፡ ለዚህም ትንተና የንፅፅር ትርጓሜ ህግ ስለሚያስፈልግ የሚከተለውን ህግ በመጠቀም ይሆናል ፡፡

**ሰንጠረዥ 25፡ የፈተና 1 እና ፈተና 2 ጥያቄዎች ውጤት ናሙናዎች ቲ - ቴስት**

| | | የሌቨን የልይይቶች እኩልነት መሞከሪያ | | የአማካይ እኩልነት ቲ - ቴስት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የ F ዋጋ | ጉልህነት | የ t ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | ጉልህነት(ባለሁለት ጫፍ | የአማካይ ልዩነት | መደበኛ የስህተት ልዩነት | 95% የልዩነት የመተማመኛ ገደቦች | |
| | | | | | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| አማርኛ | እኩል ልይይት ይኖራል | .063 | .803 | -1.650 | 42 | .106 | -2.227 | 1.349 | -4.951 | .496 |
| | እኩል ልይይት አይኖርም | | | -1.650 | 41.913 | .106 | -2.227 | 1.349 | -4.951 | .496 |
| ጉራጊኛ | እኩል ልይይት ይኖራል | .046 | .830 | -2.773 | 54 | .008 | -2.714 | .979 | -4.677 | -.752 |
| | እኩል ልይይት አይኖርም | | | -2.773 | 53.987 | .008 | -2.714 | .979 | -4.677 | -.752 |
| ኦሮምኛ | እኩል ልይይት ይኖራል | .787 | .381 | -2.869 | 38 | .007 | -2.900 | 1.011 | -4.946 | -.854 |
| | እኩል ልይይት አይኖርም | | | -2.869 | 37.137 | .007 | -2.900 | 1.011 | -4.948 | -.852 |
| ከንባትኛ | እኩል ልይይት ይኖራል | .941 | .345 | -.303 | 18 | .765 | -.600 | 1.981 | -4.762 | 3.562 |
| | እኩል ልይይት አይኖርም | | | -.303 | 16.903 | .766 | -.600 | 1.981 | -4.781 | 3.581 |

ምንጭ የ SPSS ውጤት፣ 2023

በሠንጠረዥ 25 በተገለፁት ቡድኖች መካከል ያለውን ልዩነት ለማጥናት በአማርኛ ፈተና ላይ የተካሄደው ነጻ የናሙና ቲ-ምርመራ (t — test) አስፈላጊ የሆኑ ምልከታዎችን ይፋ አድርጓል። ቢሆንም ቀጥታ ወደ ንፅፅር ትንተናው ውጤት ከመግባታችን በፊት ከአራቱ የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች አንፃር በእያንዳንዱ አምድ የተገኙትን አሃዞች ትርጉም እንደሚከተለው ይገለፃል። የሌቨን የልይይቶች እኩልነት መሞከሪያ አምድ ስር ያሉት አሃዞች የሚያሳዩት በነጻ የናሙና ቲ-ምርመራ (t — test) ውጤትን ለንፅፅር ከመጠቀም በፊት መሟላት ያለበትን መስፈርት የሚገልፁ ናቸው። በዚህም መሰረት የሌቨን ቲ - ቴስት ውጤት የp ዋጋ (የጉልህነት ዋጋ) ከ.05 ከበለጠ የነጻ ናሙናዎች ቲ - ቴስት ለንፅፅር ብቁ እና ተቀባይነት ይኖረዋል፤ ነገር ግን የp ዋጋ (የጉልህነት ዋጋ) ከ.05 ያነሰ ከሆነ ሌላ አማራጭ ወደ መጠቀም ይኬዳል ማለት ነው። በዚህም መሰረት የአራቱም የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች ተማተሪዎች የp ዋጋ .803፣ 830፣381፣345 ስለሆኑ ንፅፅሩን ማድረግ ይቻላል።

በዚህ እሳቤ መሰረት አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች በፈተና 1 እና በፈተና 2 መካከል የጎላ ልዩነት አልታየም። ምክንያቱም የነፃ ናሙናዎች ቲ - ቴስት ውጤት $t(42) = -1.650$, $p = .106 > .05$ ስለሆነ ። በተመሳሳይ በከንባትኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋ በፈተና 1 እና በፈተና 2 መካከል የጎላ ልዩነት አልታየም። ምክንያቱም የነፃ ናሙናዎች ቲ - ቴስት ውጤት $t(18) = -.303$, $p = .765 > .05$ ስለሆነ። ነገር ግን በጉራጊኛ እና በኦሮምኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በፈተና 1 እና በፈተና 2 መካከል ትርጉም ያለው የጎላ ልዩነት ታይቷል። ምክንያቱም የሁለቱም የነፃ ናሙናዎች ቲ - ቴስት ውጤት በተከታታይ $t(54) = -2.773$, $p = .008 < .05$ እና $t(38) = -2.869$, $p = .007 < .05$ ስለሆነ። ከዚህ መረዳት የሚቻለው በጉራጊኛ እና በኦሮምኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በተመሳሳይ ይዘት ፈተናዎች ሲፈተኑ የውጤት ለውጥ እንደሚያሳዩ ነው።

በአጠቃላይ የሰዋስው እዉቀትን ከተማሪዎች ቋንቋ ዳራ አንፃር ለመመዘን ከተሰጡት ሁለት ፈተናዎች አምስት የጥያቄ አይነቶች የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ከሌሎች የተሸለ ዉጤት እንዳመጡ መረጃው ያመላክታል።

## ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች

### 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በህዳሴ ፍሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሰዋስው ትምህርት አተገባበር ውጤታማነት ከቋንቋ ዳራ አንጻር መፈተሽ ነው ፡፡ ለዚህም በሰነድ ፍተሸ ፣በጽሁፍ መጠይቅ ፣በምልከታና በፈተና አማካኝነት የመምህራን የትምህርት ዝግጅት ፣አተገባበር ፣የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ፣ለሰዋስው ትምህርት ያላቸው አመለካከትና የክፍል ውስጥ ተሳትፎና በፈተና መረጃ ተሰብስቧል ፡፡የተሰበሰቡትም መረጃዎች አደራጅቶ በመተንተን የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል ፡፡

መምህራን ሰዋስው በክፍል ውስጥ ለማስተማር በሚዘጋጁበት ወቅት ተገቢነት ያለው ይዘት፣ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ ተግባቦት ያከናውኑ ዘንድ ተማሪውን ማዕከል ያደረጉ መልመጃዎችንና ተተግባሪነት ያለው አላማ ማዘጋጀት አለባቸው ፡፡ ይሁንና ጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የሚዘጋጁበት ሰዋስው ይዘት የተማሪዎች የዕለት ከዕለት ትምህርት፣ ከመጡበት ማህበረሰብና ክፍል ደረጃ ጋር የመመጣጠን አቅሙ አነስተኛ ነው ፡፡ መልመጃዎቹና ምሳሌዎቹ ቋንቋውን ከማሳወቅ ውጭ ተማሪዎች ማዕከል የማያደርጉና አሳታፊነት የጎደላቸው እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል ፡፡ በተጨማሪም መምህራኑ በአንድ ክፍለ ጊዜ ሁለት ዓላማ ይዘው የሚገቡ ሲሆን ተተግባሪነቱም መካካለኛ ነበር ፡፡

መምህራና የሰዋስው ይዘቱን ርቱዕ ወይም ኢ-ርቱዕ የማቅረቢያ ስልትን ተጠቅመው ማቅረብ ይችላሉ፡፡ ከእነዚህ ሁለት ማቅረቢያ ስልቶቸ መካከል አንዱን ወይም ሁለቱን አጣምሮና መርጦ ለመጠቀም የተማሪዎቹ የትምህርት ደረጃና የሰዋስው ይዘቱ ይወስነዋል ፡፡ የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ስንመለከት አማርኛ ቋንቋ አፈፊትና ኢ -አፈፊት ተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ ይገኛሉ ፡፡ ኢ-አፈፊት ተማሪዎች ለቋንቋ ያላቸውን ተጋልጦ ዝቅተኛ በመሆኑ ለነዚህ ተማሪዎች የተለያዩ ምሳሌዎች በመስጠት ተግባቦታዊ በሆነ መንገድ ኢ-ርቱዕ ስልት ማስተማር እንዳለባቸው ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከምልከታውና ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ሚያመለከቱት መምህራን በአብዛኘው ርቱዕ ስልት እንደሚጠቀሙ ነው ፡፡

ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው ተጠቅመው ተግባቦት ያከናውኑ ዘንድ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ግልጽ፣ አሳታፊና አፍላቂ በሆነ መንገድ መቅረብ አለበት ፡፡ ከዚህ አንጻር የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ስንመለከት አሳታፊና አፍላቂ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ቋንቋውን ተጠቅመው ተግባቦት የሚያከናውኑበት አጋጣሚ መካከለኛ ነበር ፡፡

የሰዋስው ትምህርት ዓላማ ስለታላሚው ቋንቋ ሰዋስው ህግጋት ከማሳወቅ በተጨማሪ የቋንቋውን ክሂሎች ማዳበር ነው፡፡ ለዚህም መምህራን ትምህርት ከቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅተው ማቅረብ ይኖርባቸዋል ፡፡ ይህን አስመልክቶ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ መምህራን ትምህርቱን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅተው እንደሚያስተምሩ ያሳያል ፡፡ ይህ የመምህራኑ ጠንካራ ጎን በመሆኑ የሚበረታታ ነው ፡፡

የሰዋስው መዋቅር ቅርጽ ፣ፍቺና አጠቃቀም በምናስተምርበት ወቅት በክፍል ውስጥ ከክፍል ያሉ አውዶች መጠቀም ተማሪዎች በትምህርቱ ላይ የሚኖራቸውን ተነሳሽነት ከፍ እንደሚያደርግ በክለሳ ድርሳናት አይተናል፡፡ በመሆኑም የመምህራኑን የአውድ አጠቃቀም ተገቢነት በተመለከተ በምልከታ ለማየት እንድተሞከረው የሰዋስው ይዘቱ በዐውድ ሲቀርብ አልተስተዋለም ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ድጋፍ ሰጪ የሆኑ መሳሪያዎችን እንደማይጠቀሙ የጥናቱ ዉጤት ያመላክታል ፡፡

የዚህ ጥናት አንዱ ክፍል የመምህራንን ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ መፈተሽ ነው ፡፡ በመሆኑም የመምህራኑን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በጽሁፍ መጠይቅ አማካኝነት ለመቃኘት እንደተሞከረው በክፍል ውስጥና በቤት ስራ መልክ የሚሰጡ መልመጃዎችን በተመለከተ መምህራኑ የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ ተዘውታሪነት የጎደለው እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ያመላክታል፡፡

የመማር ማስተማር ሂደትን ውጤታማ ለማድረግ ተማሪዎቹ ለትምህርቱ የሚኖራቸው ፍላጎት ፣ተሳትፎና ዕውቀት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ፡፡ይህን ተሳትፎና ዕውቀት ለማጣራት እንደተሞከረው የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ ነው፡፡ በተጨማሪም በምልከታ እንደታየው ህግጋቱ ተማሪዎች ከዚህ በፊት ካላቸው ዳራ ዕውቀት ጋር ያለው ተጣጥሞሽ ዝቅተኛ እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያመለክታል ፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሰዋስው ትምህርት አተገባባር ዉጤታማነት ከቋንቋ ዳራ አንጻር መፈተሽ ነው ፡፡ በመሆኑም በአማርኛ ፣ ጉራጊኛ፣ኦሮምኛ እና ከንባትኛ ቋንቋ አፌፊት ተማሪዎች በተሰጣቸው ፈተና 1 እና ፈተና 2 ዉጤት ቲ-ቴስት ትንተና እንደሚያመላክተው አማርኛ ቋንቋ አፌፊት ተማሪዎች ከሌሎች የተሸለ ውጤት ያስመዘገቡ መሆኑን የትንተናው ዉጤት አመላክቷል ፡፡ ይሁን እንጅ የአማርኛ ቋንቋ አፌፊት የሆኑ ተማሪዎችም ቢሆኑ ያመጡት ውጤት ይበል የሚያሰኝ ሆኖ አልተገኘም ፡፡

## 5.2 የመፍተሄ ሃሳቦች

መምህራን የሰዋስው ትምህርት በሚያስተምሩበት ወቅት የሚጠቀሙበት የማስተማሪያ ብልሀቶች በተማሪዎች የተግባቦት ብቃት ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽኖ ያሳድራል ፡፡ በመሆኑም በምዕራፍ አምስት ላይ የታዩትን ችግሮች አስወግዶ የመማር ማስተማሩን የተሻለ ለማድረግ የሚከተሉት የመፍትሄ ሃሳቦች ቀርበዋል ፡፡

- ✓ መምህራኑ በትምህርት ዝግጅታቸው ወቅት ከተማሪዎች የክፍል ደረጃ ፣እድሜና ከመጡበት ማህበረሰብ ጋር የሚሄድ ይዘት ቢዘጋጁ ፡፡ ዓላማው ውስን ቢሆን በተጨማሪ የሚቀርቡት ምሳሌዎችና መልመጃዎች ተማሪውን ማዕከል ያደረጉና አሳታፊነት ያላቸው ቢሆኑ ተመራጭ ይሆናል ፡፡
- ✓ መምህራን የሰዋስው ትምህርት አቀራረበቸው ግልፅ አሳታፊና አፍላቂ በሆነ መንገድ ቢቀርብ ፡፡
- ✓ መምህራን ሰዋስውን ሲያስተምሩ ህግጋቱ ተማሪዎች ከዚህ በፊት ካላቸው ዳራዊ ዕውቀት ጋር እየተጣጣመ ቢቀርብ የተሻለ ነው ፡፡

- ✓ መምህራን  ሰዋስውን ሲያስተማሩ ተማሪዎች የቋንቋውን ቅርፅ ፣ፍቺና ማህበራዊ አጠቃቀም በቀላሉ ይረዱ ዘንድ ከክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ ያሉ አውዶችን ቢጠቀሙ ፡፡
- ✓ ከዚህ በተጨማሪ ደጋፊ የሆኑ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ቢጠቀሙ የተሻለ ይሆናል ፡፡
- ✓ መምህራን የተለያዩ የሰዋስው ህግጋትን ሲያቀርቡ ምሳሌዎችን በአውዱ አስደግፈው በማቅረብ ተማሪዎቹ እንዲወያዩ በማድረግ የሰዋስው ህግጋት ለይተው እንዲያወጡ በማድረግ ከክሂሎች አቀናጅተው ቢያስተምሩ ፡፡
- ✓ የአፍልቆት ደረጃ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፃነት የሚገልጹበት በመሆኑ መምህራን ተማሪዎች የሚፈጽሙትን ስህተት በማስታወሻ በመያዝ በመጨረሻ ላይ አርማት ቢሰጡ፡፡ በተጨማሪም የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ ተዘውታሪነት ያለውና ሁሉንም ያማከለ ቢሆን ነው፡፡
- ✓ የተለያዩ የሰዋስው መልመጃ ብልሃቶች ተጠቅሞ ማስተማር ተማሪዎች በትምህርቱ ላይ በንቃት እንዲሳተፍና የታላሚውን ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ህግጋት በቀላሉ እንዲረዱ ስለሚያደርጉ የሰዋስው ማለማመጃ ብልሃቶችን ቢጠቀሙ  ፡፡
- ✓ መምህራን በክፍል ውስጥ በሚያስተምሩበት ወቅት በተለያየ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች መኖራቸውን ከግንዛቤ በማስገባት የተለያዩ አውዶችን  ቢጠቀሙ ፡፡
- ✓ በማጠቃለያው ክፍል የተገለጹት  በትምህርቱ  አተገባበር ላይ የታዩት ተያያዥነት ያላቸው ችግሮች ሲሆን ዋንኛውና መሠረታዊ ችግር ግን በሰነድ ፍተሻ ወቅት ለማየት እንደተሞከረው የትምህርት ፖሊሲው  ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ትኩረት ባለመስጠቱ ምክንያት ለትምህርቱ በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ ብቻ መሰጠቱ ችግሩን ሊቀርፈው ስለማይችል የሚመለከተው ክፍል ማሻሻያ ቢያደርግ ችግሩን ሊፈታ ይችላል፡፡
- ✓ በተጨማሪ የዚህ ጥናት ግኝት ከዚህ የሰፋ እንድምታ እንዲኖረው ሌሎች አጥኝዎች ተጨማሪ ጥናቶች ቢያካሄዱ መልካም ነው ፡፡ ተጨማሪ ጥናቶች መካሄዳቸው የዚህ ጥናት ዉስንነት በመቅረፍ የውጤቱን እንድምታ ያሰፋዋል ፡፡

## ዋቢዎች

ህልፍቲ ተካ (2004) ፡፡ « የሰዋስው የዘቶችን በማስተማር የአሳታፊ የማስተማሪ ዘዴ አተገባበር ፍተሻ ፡፡ » አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፡፡ በኤም .ኤ.ዴግሪ ማሟያ የተጠና ፡፡ (ያልታተመ)

በላይነህ ሀይሌ (2003) ፡፡ « የሰዋስው ትምህርት አተገባበር ፍተሻ ፡፡ » (በሀድያ ዞን

በተመረጡ ሶስት የስምንተኛ ክፍል ትምህርት ቤቶች ናሙናነት ) አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ ለኤም.ኤ.ዴግሬ ማሟያ ፡፡ (ያልታተመ) ፡፡

ባየ ይማም (2000)፡፡ የአማርኛ ሰዋስው ፡፡የተሻሻለዉ ሁለተኛ እትም አዲስ አበባ ተ.መ.ማ.ድ.የተ.የግ.ማህበር

እሱሌማን አባይ (2003)፡፡ « በአስራ ሁለተኛ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ ፡፡» ከስነ ትምህርታዊ ሰዋስው

አንጻር ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኤም.ኤ.ዴግሪ ማሟያ ፡፡ (ያልታተመ ) ፡፡

ጌታሁን አማረ (1989) ፡፡ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ አስረኛ እትም ፣ አዲስ አበባ ፣ አልፋ ማተሚያ ቤት

Atkins J. hallom B and B and Nuru M .(1995). Skills Development Methodology , Addis Ababa : Addis Ababa University press.

Brown ,D. (1994) . principles of Language and Teaching Practice and theory .cambridge

Bygate,M, Allan Tonkya and Eddie Williams (ed .) (1994 ) .Grammer and the Language Teacher .Prentice Hall International UHLtd.

celce-Mureia .M.(1991). Grammer Pedagogy in guaratarly.25(3),459-480

Canning sworth . A. (1984). Evalaluating and Selecting ELT Teaching Material .Oxford: Heinman book Ltd

Ellis.R . (2000). « The place of Grammar in instruction in the second / foreign language curriculum» in Brown.K.(ed) language and linguistics. Ency clopedia vol.g.oxford : Elsevier Hd. (pp 28-54)

Grant ,N.(1987). Making most of your Text Book .London:Log man: long man

Hamer,J,(1987).Teaching and learning Grammar .London :Longman group .

Krashen,S.(1995). Principles and Practice in second Language Acquisition .London :Prentice Hall Macmillan .

Larsen –freeman . D.(1986) .Techniques and Principles In Language Teaching.Oxford ,Oup.

Mahmmood Salami (2008). « Goals and Technigues For Teaching Grammer.» online , http://www.ask com/bar 20/5/23 3:40 Am

Michell,R. 1994 ''Grmmar and Teaching'' in Bygate, M . Tonkyn,A and Williams, E.(ed). Grammar and the Language Teachers New York : prentice Hall 215-223

Mirosolow (2004). « On The Effectiveness of options in Grammar Teaching .»online : http://www.the free liarray,com.Accessed 23/5/23 -2:33 Am

Ur.p. (1988).Grammar Practices activies .cambridge ,cue

Widodo , H.(2006), «Approches and procedures for Teaching Grammar.(http) education Waikato.ac.nz/files/etpc/2006 V5n 1.ppt pp 122-141 at 18/5/2023 10:5 Am

## አባሪ 1 በተማሪዎች የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ

በዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በህዳሴ ፍሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል የሰዋስው ይዘቶችን በመማር ማስተማር ሂደት እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን ከተማሪዎች መረጃ ለመሰብሰብ ነው ፡፡ በመሆኑም ከመጠይቁ የሚገኘው ውጤት ለተጀመረው ጥናት መሳካት ከፍተኛ እገዛ ስላለው አንተ/አንቺ በመጠይቁ ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች በማንበብ ተገቢውን መልስ በመስጠት እንድትተባበሩን በትህትና እጠይቃለሁ ፡፡

**ማሳሰቢያ** ፡- በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

1. አጠቃላይ መረጃ

   1 ትምህርት ቤት ____________________

   2. የአፍ መፍቻ ቋንቋ __________________

   3 ሁለተኛ ቋንቋ ______________________

2 የሰዋስው ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ አምስት አማራጮች ቀርበዋል ፡፡ ስለዚህ ከምርጫው አንዱን ብቻ በመምረጥ በመረጥከው /ሽው ቁጥር ይህንን (✓) ምልክት በማስቀመጥ መልስህን/ሽን አመልክት/ቺ ፡፡

ምርጫዎቹ

5.በጣም ከፍተኛ

4.ከፍተኛ

3.መካከለኛ

2.ዝቅተኛ

1.በጣም ዝቅተኛ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የሰዋስው ትምህርት ዓላማ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተያያዥነት አለው ? | | | | | |
| 2 | መምህርህ/ሽ ሰዋስውን ለምን እንደምትማር/ሪ አዘውትረው ይገልፃሉ? | | | | | |
| 3 | የአማርኛ ሰዋስውን ለመማር ፍላጎት አለህ /ሽ ? | | | | | |
| 4 | መምህራችሁ በክፍል ውስጥና በቤታችሁ እንድትሰሩ የሚሰጧችሁ የሰዋስው መልመጃዎች አዘውትረው ያርማሉ ? | | | | | |
| 5 | መምህርህ /ሽ/ በክፍል ውስጥም ሆነ በቤት ስራ መልክ አጫጭር ድርሰቶችን እየጻፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ እንድታነቡ ይደረጋል ? | | | | | |
| 6 | በመማሪያ መፅሐፍህ/ሽ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው መልመጃዎች ከባድ ናቸው ? | | | | | |
| 7 | መምህራን ሰዋስውን የሚያስተምሩት ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ነው ? | | | | | |
| 8 | መምህርህ/ሽ/ የሰዋስው ትምህርት ሲያቀርቡላችሁ የትምህርት መርጃዎችን ይገልፃሉ ? | | | | | |
| 9 | መምህራችሁ የሚያቀርበው /የምታቀርበው /ሰዋሰዋዊ ይዘት ካላችሁ ዳራዊ ዕውቀት ጋር ያለው ተጣጥሞሽ ምን ይመስላል ? | | | | | |
| 10 | መምህራችሁ የሰዋስው ትምህርትን ስትማሩ ትኩረታችሁን ትምህርቱ ላይ እንድታደርጉ ምን ያህል ያበረታታሉ? | | | | | |

**አባሪ ሁለት**

**በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ትምህርት**

**የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**

**የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ምልከታ ቅፅ**

- ✓ ምልከታ ------------------------
- ✓ የትምህርት ቤቱ ስም --------------------------------
- ✓ ፈረቃ------------------------------------
- ✓ ምልከታ የተደረገበት ቀን --------------------------
- ✓ የትምህርቱ ርዕስ -----------------------------------
- ✓ የዕለቱ ትምህርት አላማ ---------------------------

| ተ.ቁ | የሚተኮርባቸው ነጥቦች | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም አነስተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 1 | የሰዋስው ይዘቱ ከተማሪዎች ዳራ ጋር ያለው ተጣጥሞሽ ምን ይመስላል | | | | | | | | | | |
| 2 | የድጋፍ ሰጭ መሳሪያዎች ምርጫና አተገባበር | | | | | | | | | | |
| 3 | ህግጋቱ ተማሪዎች ከዚህ በፊት ካላቸው ዳራዊ እውቀት ጋር ያለው ተጣጥሞሽ | | | | | | | | | | |
| 4 | በልምምድ ደረጃ የመምህሩ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ | | | | | | | | | | |
| 5 | በአፍልቆት ደረጃ የመምህሩ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ | | | | | | | | | | |
| 6 | ምጋቤ ምላሹ ሁሉንም ተማሪዎችን ማማከሉ | | | | | | | | | | |
| 7 | ተማሪዎች በትምህርቱ ወቅት የነበራቸው ሚና | | | | | | | | | | |
| 8 | መምህሩ የሚያቀርባቸው ምሳሌዎች ብዛትና መልመጃዎቹ ተማሪዎችን የማመራመር ደረጃና ተግባቦትን ለማከናወን ያለው ሚና | | | | | | | | | | |
| 9 | ለልምምድ የቀረቡ ብልሃቶች ተገቢነት | | | | | | | | | | |
| 10 | በአፍልቆት ጊዜ የመምህሩ ጣልቃ ገብነት | | | | | | | | | | |

## አባሪ 3 ፈተና አንድ

በህዳሴ ፍሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለአስርኛ ክፍል መቶ ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ዕውቀታቸው ለመመዘን የተሰጠ ፈተና ።

ለፈተናው የተፈቀደ ጊዜ 1:30

የመፈተኛ ቦታ -----------------------------

የተፈታኝ መለያ ቁጥር--------------------

አጠቃላይ መመሪያ ፡- ይህ ፈተና የሰዋስው ዕውቀትን ለመለካት የቀረበ ነው። ጥያቄዎቹ በአምስት መመሪያዎች ተከፋፍለው ቀርበዋል ። የመጀመሪያው ክፍል አስራ አምስት የተለያዩ ሰዋስዋዊ የምርጫ ጥያቄዎችን ይዟል። ሁለተኛው ክፍል አምስት ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን ቃላትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል ለቃላቱ የሚስማሚቸውን በመምረጥ የሚመለሱ ናቸው ። በሶስተኛው ክፍል የተሰጡትን አምስት ቃላት በመጠቀም የተለያዩ የዓረፍተ ስልቶችን የማዋቀር ጥያቄዎች ቀርበዋል። በአራተኛው ክፍል አምስት ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን ለተሰጡት ቃላት እማራዊና ፍካሪያዊ ፍቺዎችን የሚጠይቁ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ሁሉንም ጥያቄዎች ለመመለስ የተሰጠው ጊዜ 1 ሰዓት 30 ደቂቃ ሲሆን የሚታረመው 50 % ነው ። መልሶቻችሁን በተሰጣችሁ የመልስ መስጫ ወረቀት ሊነበብ በሚችል ጽሑፍ መልሱ ።

መመሪያ አንድ ፡- ከጥያቄ ቁጥር 1 እስከ 15 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል ። ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ 15%

1. ከሚከተሉት ስሞች መካከል "ኦች" የሚለውን ቅጥያ በመውሰድ የሚበዛው ቃል የትኛው ነው ?
   ሀ. አሸዋ ለ. ሴት ሐ. ወተት መ. ዝናብ
2. "ዳልቻ"የሚለው ቃል የአማርኛ ቋንቋ ከኦሮምኛ ቋንቋ የተወሰደ ነው ብንል ክስተቱ ምን ይጠቁማል ?
   ሀ. ቋንቋ ምሉዕ መሆኑን ሐ. ቋንቋ ዘረቀዳዊ መሆኑን
   ለ. የቋንቋ አንዱ ባህሪ መሆኑን መ. የቋንቋ አንዱ ባህሪ ስርዓታዊነት መሆኑን
3. «ከበደ ከአዋሳ ቶሎ መጣ ።» በሚለው ዓረፍተ ነገር የተሰመረበት ቃል በየትኛው የቃል ክፍል ይመደባል ?
   ሀ. ስም ለ. ተወሳከ ግስ ሐ ቅፅል መ መስተዋድድ
4. እፎይ ! ገና አሁን ትንሽ ሻል አለኝ ። የሚለው ዓረፍተ ነገር በየትኛው የዓረፍተ ነገር ስልት የተዋቀረ ነው?
   ሀ. በትእዛዛዊ ለ. በሐተታዊ ሐ. በማጋነን/ቃል አጋኖ መ. በመጠይቅ
5. ከሚከተሉት ውስጥ ባለንብረትነቱ የእሱ መሆን የሚያመለክተው ግስ የትኛው ነው ?
   ሀ. ቤትህ ለ. ቤትሽ ሐ. ቤቷ መ. ቤቱ

6. «እናቴ <u>የጠላውን</u> አተላ ደፋችው:: » በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ በተሰመረበት ቃል ውስጥ ያለው "ን" ተግባሩ ምንድነው ?
ሀ. ባለቤትን ማመላከት ሐ. ግስን ማመላከት
ለ. ተሳቢን ማመላከት መ. ገላጭን ማመላከት

7. ከሚከተሉት ዉስጥ ውስብስብ ዓረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው ?
ሀ. ከሁለት ሳምንት በኃላ ደብዳቤ በፖስታ ቤት መጣልኝ ::
ለ. የፈተና ዉጤቴን አውቂያለሁ ::
ሐ. የጠበቃዉ ምክር ከፍርድ ቤት ተሟግቼ እንዳሸንፍ ረድቶኛል::
መ. እኔ፣ወንድሜና ታናሽ እህቴ ምክርህን ስራ ላይ አውለናል ::

8. ከሚከተሉት ቃለት ውስጥ የእርባታ ቅጥያ ያለው የትኛው ነው ?
ሀ. ሰራተኛ ለ መንገዳችን ሐ. ተቀማጭ መ. ስብራት

9. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል አሉታዊ ዓረፍተ ነገር የትኛው ነው ?
ሀ. ሰውየው በጣም ዝምተኛ ሰው ነው:: ለ. ሴትየዋ ጠንካራ መኪና ገዛች ::
ሐ. አትሌቱ ወደ ለንደን አልሄድም መ. በመጥፎ ስነምግባሩ ይቀጣ::

10. «አንገታም » የሚለው ቃል ሁለት ፍቺ ሊሰጥ የሚችለው ምን ሲሆን ነው ?
ሀ. "ን" ጠብቆ ሲነበብ እና "ገ" ላልቶ ሲነበብ ::
ለ. "ታ " ጠብቆና ላልቶ ሲነበብ ::
ሐ."ገ " ጠብቆና ላልቶ ሲነበብ ::
መ."ን " ላልቶ ሲነበብ ::

11. የጥሬ ስጋ ማባያን እንዳንዶቹ አዋዜ፣ይሉታል ፣ሌሎች ደግሞ ዳጣ ወይም ቆጭቆጫ ይሉታል :: ይህ አሰያየም ከቋንቋ መሰረታዊ ባህሪያት መካከል ይበልጥ የቱን ያሳያል ?
ሀ. የቋንቋ ረቂቅነትን ለ. የቋንቋ ዘፈቀዳዊነት
ሐ. የቋንቋን ተዋዋሽነት መ. የቋንቋን ስርዓታዊነት

12. ውሻ የሚለው ቃል ስም ላይ --------የሚል ቅጥያ ሲጨመር የውሻው ጾታ ይታወቃል ?
ሀ. -ኣችን ለ. -ኤ ሐ. -ኦች መ. -ኢቱ

13. ከሚከተሉት ውስጥ ለተራ ዓረፍተ ነገር የትኛው ምሳሌ ይሆናል ?
ሀ. መሀመድ ጥናት ከማፍቀሩም በላይ ትሁት ነው::
ለ. ዳዊት መጠየቅና መከራከር በጣም ይወዳል ::
ሐ. መንበረ እጅግ በጣም ጨዋ በመሆኗ ሁሉም ያከብራታል ::
መ. እህተ በጣም ነቃ ያለችና አስተዋይ ተማሪ ነች ::

14. ---------------የቋንቋ መሰረታዊ ባህሪ ነው ?

ሀ. ዘላለማዊ ለ. ተዋዋሽነት ሐ. አይለወጤነት መ. አይለመዴነት

15. «አባቴ ብዙ ደክሞ የሰራው ቤት በአነስተኛ ዋጋ ተሸጠ ፡፡» የሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ያለውስ ግሳዊ ሀረግ --------- ነው ?

ሀ. በአነስተኛ ዋጋ ለ. አባቴ ብዙ ደክሞ ሐ. በአነስተኛ ዋጋ ተሸጠ መ. የሰራው ቤት

*መምሪያ ሁለት ፡- ከተራ ቁጥር 16 እስከ 20 ድረስ ቃላት የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ለእያንዳንድ ጥያቄ ትክክል የሆነውን ምልስ ምረጥ /ምረጭ (5 ነጥብ)*

16. "ንፉግ" በሚለው ቃል ላይ "ነት " የሚል ቅጥያ ምዕላድ ሲጨመር የሚገኘው ቃል ፍቺ ምን ይሆናል ?

ሀ. የማይሰጥ ለ. የሚሰጥ ሐ. ገብጋባ መ. መሰሰት

17. "ዘልቋል" የሚለው ቃል "ተዳርሷል የሚለው ፍቺ እንዲኖረው የሚያደርገው የትኛው ዓረፍተ ነገር ነው ?
ሀ. ምስማሩ ወደ ወስጥ ገብቷል ለ. ወሬው አገር ቤት ዘልቋል
ሐ. ልጁ በትምርት ዘልቋል መ. እንግዳው ወደ ዉስጥ ዘልቋን

18. «የሰርጉ ደጋሾች ከተጠሩ እንግዶች ይልቅ ቋሚዎችን ለማብላት ቅድሚያ ሰጡ » በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ዐዉዳዊ ፍቹ ምንድን ነው ?
ሀ. አስተናጋጂ ለ. በህይወት ያሉ ሐ. ቆመው የሚውሉ መ. የማይለዉጡ

19. በልጆቻቸው አለመግባባት መካከል በተፈጠረው ግጭት አሁን ደመኛ ሆነዋል ፡፡ የተሰመረበት ቃል በፍቺ ሚቃረነው ቃል የትኛው ነው ?

ሀ. ባላጋራ ለ. ወዳጅ ሐ. አማች መ. አበልጅ

20. የገጠሩ ተማሪ «ቲክኖሎጂን በተመለከተ ባይተዋር ስለሆነ ተጨማሪ ስልጠና ያስፈልገዋል » ፡፡ የተሰመረበት ቃል በፍቺ ሊተካው የሚችለው---------ነው፡፡
ሀ. እንግዳ ለ. መጤ ሐ.ፈሪ መ. አስተዋይ

*መመሪያ ሶስት ፡- ከተራ ቁጥር 21 እስከ 25 የቀረቡትን ቃላት በመጠቀም ሰዋስዋዊ ስርዓታቸውን የጠበቁና ተገቢ ስርዓት ነጥቦች ያሚሉ አንዳንድ ሀተታዊ ፣ጥያቄያዊ ፣ትዕዛዛዊ ፣አጋናኝ አውንታዊና አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች መስርቱ ፡፡(5%)*

21. ወደቀ (ሐተታዊ)
22. ፈጣን (ጥያቄያዊ)
23. ቆራጣ (ትዕዛዛዊ)
24. ተገነባ (አጋናኝ)
25. ተመቸ (ሐተታዊ/አሉታዊ)

መመሪያ አራት ፡- ከተራ ቁጥር 26-30 ለቀረቡት ቃላት እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡(10%)

| | እማሪያዊ | ፍካሪያዊ |
|---|---|---|
| 26. ዶማ | ------------------- | -------------------- |
| 27. መሬት | --------------------- | -------------------- |
| 28. እርግብ | --------------------- | -------------------- |
| 29 አመድ | --------------------- | -------------------- |
| 30. መብረቅ | --------------------- | -------------------- |

መመሪያ አምስት ፡- በተሰጡት ዐ.ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ሀረጎች መሪ ቃልና የሀረጎችን አይነት ጻፍ /ፊ ፡፡ (10%)

1. አያና የእግር ኳስ ጨዋታ ለመመልከት እስቴዲዮም ገባ ፡፡
2. የትምህርት ቤታችን የስፖርት መምህር የአትሌቲክስ ውድድር እንደሚያዘጋጁ ነገሩን::
3. ሁሉም ሰው እንደ ንብ ታታሪ ሰራተኛ መሆን አለበት ፡፡
4. በቃጠሎው በጣም የተጎዱ ቤቶች ፈርሰው በአዲስ መልክ እንደ ገና ተሰሩ ፡፡፡
5. ትናንት ገበያ ውስጥ ያየነው እብድ ተይዞ ወደ አዕምሮ ሆስፒታል ተወሰደ ፡፡

**መልካም ዕድል !!**

አባሪ 4 ፈተና ሁለት

በህዳሴ ፍሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለአስርኛ ክፍል መቶ ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ዕውቀታቸው ለመመዘን የተሰጠ ፈተና ።

ለፈተናው የተፈቀደ ጊዜ 1:30

የመፈተኛ ቦታ -----------------------------

የተፈታኝ መለያ ቁጥር--------------------

አጠቃላይ መመሪያ ፡- ይህ ፈተና የሰዋስው ዕውቀትን ለመለካት የቀረበ ነው። ጥያቄዎቹ በአምስት መመሪያዎች ተከፋፍለው ቀርበዋል ። የመጀመሪያው ክፍል አስራ አምስት የተለያዩ ሰዋስዋዊ የምርጫ ጥያቄዎችን ይዟል። ሁለተኛው ክፍል አምስት ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን ቃላትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል ለቃላቱ የሚስሟሟቸውን በመምረጥ የሚመለሱ ናቸው ። በሶስተኛው ክፍል የተሰጡትን አምስት ቃላት በመጠቀም የተለያዩ የዓረፍተ ስልቶችን የማዋቀር ጥያቄዎች ቀርበዋል። በአራተኛው ክፍል አምስት ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን ለተሰጡት ቃላት እማራዊና ፍካሪያዊ ፍቺዎችን የሚጠይቁ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ሁሉንም ጥያቄዎች ለመመለስ የተሰጠው ጊዜ 1 ሰዓት 30 ደቂቃ ሲሆን የሚታረመው 50 % ነው ። መልሶቻችሁን በተሰጣችሁ የመልስ መስጫ ወረቀት ሊነበብ በሚችል ጽሑፍ መልሱ ።

መመሪያ አንድ ፡- ከጥያቄ ቁጥር 1 እስከ 15 ድረስ የተለያዩ ሰዋሰዋዊ ጥያቄዎች ቀርበዋል ። ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ 15%

1. "አለሚቱ ደብረብርሃን <u>ሰንብታ</u> መጣች ።" በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ የተሰመረበት የትኛውን ያመላክታል ?

ሀ. ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አነስታይ  ሐ. ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባዕተይ
ለ. ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አነስታይ  መ. ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባዕተይ

2. ካብረቅራቂው መጋረጃ በስተጀርባ መኝታ ቤት ይገኛል ። የዚህ ዐ.ነገር ባለቤት የትኛው ነው ?

ሀ. በስተጀርባ መኝታ ቤቱ  ሐ. ካብረቅራቂው መጋረጃ በስተጀርባ
ለ. መኝታ ቤቱ  መ. ካብረቅራቂው መጋረጃ

3. ድምጾች ተቀናጅተው ቃላትን የሚመሰርቱበት የቋንቋ ባህሪ -------ተብሎ ይጠራል ።

ሀ. ዘፈቀደኝነት  ለ. ስርዓተኝነት  ሐ. ምዕሉነት  መ. ሰብዓዊነት

4. ከመጠን በላይ መመገብ <u>ቁንጣን</u> ያስይዛል ። በተሰመረበት ቃል ላይ መድረሻ ምዕላድ ሆኖ ቢቀጥል ቃሉን ቅጽል ሊያደርግ የሚችለው የትኛው ነው ?

ሀ. -ኡ  ለ. -አም  ሐ. -ነት  መ.-ኦች

5. "መምህራን" የሚለውን ቃል መሰረት በማድረግ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. የጥገኛ ምዕላዱ ፋይዳ አብዥነት ነው ፡፡ ሐ. ጥገኛ ምዕላዱ /-ራን/ነው ፡፡

ለ. ጥገኛ ምዕላዱ ፋይዳ ራሱን የቻለ የይዘት ፍቺ አለው ፡፡ መ.ነፃ ምዕላዱ ቅጽል ነው፡፡

6. ያ በጣም ጎበዝ የክፍላችን አለቃ በከፍተኛ ውጤት ተመረቀ ፡፡ በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ ግሳዊ ሀረጉ የትኛው ነው ?

ሀ. የክፍላችን አለቃ በከፍተኛ ውጤት ለ. አለቃ በከፍተኛ ውጤት

ሐ. ያ በጣም ጎበዝ የክፍላችን አለቃ መ. በከፍተኛ ውጤት ተመረቀ

7. «ማንኛውም ቋንቋ በራሱ ምሉዕ ነው» ስንል ምን ማለታችን ነው ?

ሀ. ከሌሎች ቋንቋዎች በመዋስ ጉድለቱን ይሞላል ማለታችን ነው ፡፡

ለ. በትርጉም የሌላውን ቋንቋ ሀሳብ ማስተላለፍ ያስችላል ማለታችን ነዉ፡፡

ሐ. ሙሉ በሙሉ እራሱን የቻለ ነው ማለታችን ነው ፡፡

መ. የተናጋሪው ባህል መግለጽ ይቻላል ማለታችን ነው፡፡

8. የአሁን ትውልድ ሩቅ <u>አላሚ</u> እንደሆነ ይነገርለታል ፡፡ የተሰመረበት ቃል የተመሰረተው ከየትኛው ቃል ነው ?

ሀ. አለመ ለ. አለም ሐ. እልም መ. ኢላማ

9. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ነው ፡፡

ሀ. በእኔና በእናቴ ላይ ከባድ ሀዘን ወደቀብን ፡፡

ለ. ክፍላችን በእግር ኳስ ጨዋታ ዋንጫተ ሸለመ ፡፡

ሐ. ቀኑ ስለመሸ ወደ ቤታችን አልሄድንም ፡፡

መ. ጆብደኛው ወጣት በረንዳ ላይ አደረ፡፡

10. «ፈጣኑ አበበ ከወንድሙ ጋር ተግቶ አጠና » በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ መስተዋድዳዊ ሀረጉ የትኛው ነው ?

ሀ. ከ ወንድሙ ጋር ለ. ፈጣኑ አበባ ከወንድሙ ጋር

ሐ. ከ ወንድሙ ጋር ተግቶ መ. ከ ወንድሙ ጋር ተግቶ አጠና

11.ከሚተሉት በዝርዝር ከተጻፉት ቃላት መካከል መጠይቃዊ አረፍተ ነገሮችን የሚመሰርቱ ቃላት የትኞቹ ናቸው ?

ሀ. መቼ፣የት፣እንዴት ሐ. መጣሁ፣መጣሽ፣መጣችሁ

ለ. ይሀ፣ ያ፣ እነዚያ መ. እናንተስ፣እነሱስ፣ እኛስ

12."በግ" ምዕላድም ቃላትም ነው እንዲባል ያስቻለው ምንድን ነው ?
ሀ.ፍች ያለው አሃድ መሆኑ
ለ. ከእሱ ወደነሱ አሃዶች ሊከፈል የማይችል መሆኑ
ሐ. በቃልነቱ ባንዱ  የቃል ክፍል የሚመደብ በመሆኑ
መ. ሁሉም መልስ ይሆናል

13. «አቶ ከበደ ኃይለኛ ዉሻ ነከሷቸው ክፉኛ ታመዋል ።» በሚለው ዓረፍተ ነገር ዉስጥ የተሰመረበት ምንን ያመለክታል ?
ሀ. ግስ    ለ. ስም    ሐ. መስተዋድድ    መ. ተውሳከ ግስ

14. አባትዬ «እኔ ክንዴን ሳልንተራስ ጠንክረህ ብትማር ይሻልሃል !»  አሉት ። የተሰመረበት ሀረግ ትርጉም --------ነው
ሀ. ሳይደክመኝ    ለ. እጅ ሳያጥረኝ    ሐ. የአልጋ ቁራኛ ሳልሆን    መ. ሳልሞት

15. ከሚከተሉት ዓረፍተነገሮች መካከል ትክክለኛ የአያያዥ ቃል አጠቃቀም ሚታይበት የትኛው ነው?
ሀ. መሰረት ከውጭ ሀገር ዛሬ ቢሆንም  ነገ ትገባለች
ለ. አባይ ብዙ ዘመን ሸፍቶ ቆየ ይሁን እንጂ የህዝብ ጥሬ ስምቶ ተመለስ
ሐ. ልጁ በፅኑ ታሟል ። አለበለዚያ ሀኪም ቤት መሄድ አለበት
መ. ተማሪው ሌት ተቀን አጠና ነገር ግን ፈተናዉ አለፈ

መመሪያ ሁለት ፡- ከተራ ቁጥር 16 እስከ 20ድረስ ቃላትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል ። ከቀረቡት አማራጮች መካከል ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ /ረጭ (5%)

16.ህዝቡ በነቂስ ወጥቶ ሰፈሩን አፀዳ ። በሚለው ዐ.ነገር ከስሩ የተሰመረበት ቃል ተቃራኒ ፍቺ የሆነው የቱ ነው

ሀ. ሁሉም    ለ. በሙሉ    ሐ በተናጥል    መ. በጠቅላላ

17."ያ ሰውዬ ምንደኛ ነው ። " የተሰመረበት ቃል ፍቺ የሚሆነው የቱ ነው ?
ሀ. ነገረኛ    ለ. ሙለኛ    ሐ. ጦሰኛ    መ ደሞዝተኛ
18. "ሳይታክት"ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ----ነው ።
ሀ. ሳይደሰት    ለ. ሳይበሳጭ    ሐ. ሳይሰለች    መ. ሳይዝናና
19.በውድድሩ ያሸነፈ ዳጎስ ያለ ሽልማት ይጠብቀዋል ። የተሰመረበት ቃል ትርጉም ----ነው ።
ሀ. ደልድል ያለ    ለ. ጠቀም ያለ    ሐ. ኮሰስ ያለ    መ. ኮስመን ያለ
20.አንድ ሰው ማር አልስም ብሎ ከተናገረ አነጋገሩ ምንን እንደሚያመላክት ከተሰጡት አማራጮች መካከል ፈልጉ ።

*መመሪያ ሶስት የቀረቡትን ቃላት በመጠቀም ሰዋሰዋዊ ስርዓታቸውን የጠበቁና ስርዓተ ነጥቦችን ያሟሉ አንድ አንድ ሐተታዊ፣ ጥያቄያዊ ፣ትዕዛዛዊ ፣አጋናኝ ፣አዉንታዊና አሉታዊ ዓረፍተነገሮች መስርቱ ።* (5 ነጥብ )

21. ወደቀ (ሐተታዊ)
22. ፈጣን (ጥያቄያዊ)
23. ቆራጥ (ትዕዛዛዊ)
24. ተገነባ (ቃል አጋኖ)
25. ተመቸ (ሐተታዊ/አሉታዊ)

*መመሪያ አራት ፡-በተሰጡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ሐረጎች መሪ ቃልና የሀረጎች አይነት ጻፉ ።*(10 ነጥቦች)

1. ትናንት የታመመውን ተማሪ ወደ ሆስፒታል ተወሰደ ።
2. ወይኒቱ እንደ ወንድሟ በጣም ጎበዝ ተማሪ ናት።
3. አህቱ ስለመጣች ደስ አለው።
4. ጫልቱ እንደ እህቷ ቶሎ ትከፋለች
5. ሁሉን በሆዱ የሚይዝ ሰው እራሱን ይጎዳል ።

*መመሪያ አምስት ፡- ቀጥለው ለተሰጡት ቃላት እማሪያዊ እና ፍካሪያዊ ፍቺ ስጡ* (10 ነጥብ)

| | እማሪያዊ | ፍካሪያዊ |
| --- | --- | --- |
| 1. እርግብ | -------------------- | ---------------------- |
| 2. እሾህ | --------------------- | ----------------------- |
| 3. ቆቅ | ---------------------- | ----------------------- |
| 4. ምላጭ | ---------------------- | ------------------------ |
| 5. እባብ | --------------------- | ------------------------ |

*መልካም ፈተና !*

አባሪ 5 የፈተናዎች ዉጤት

*ሀ. የአማርኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ተማሪዎች የፈተና አንድ ውጤት*

| ተ.ቁ | የምርጫ ጥያቄ (15%) | ቃላትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች (5%) | ሰርዓታቸውን የጠበቁ ሰዋሰዋዊ ዓረፍተ ነገሮች መመስረት(10%) | የሐረጎች መሪ ቃላትና የሐረጎችን አይነት መፃፍ (10%) | እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍቺ መስጠት (10%) | የፈተና አንድ ድምር ውጤት (10%) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 10 | 4 | 8 | 7 | 8 | 37 |
| 2 | 9 | 4 | 7 | 8 | 8 | 36 |
| 3 | 11 | 5 | 8 | 7 | 9 | 40 |
| 4 | 7 | 4 | 6 | 8 | 8 | 33 |
| 5 | 12 | 5 | 8 | 7 | 10 | 42 |
| 6 | 10 | 4 | 8 | 7 | 8 | 37 |
| 7 | 8 | 4 | 7 | 6 | 7 | 32 |
| 8 | 6 | 3 | 7 | 6 | 8 | 30 |
| 9 | 8 | 4 | 7 | 8 | 7 | 34 |
| 10 | 10 | 4 | 8 | 7 | 8 | 37 |
| 11 | 12 | 5 | 7 | 8 | 9 | 41 |
| 12 | 10 | 4 | 9 | 8 | 8 | 39 |
| 13 | 9 | 3 | 7 | 8 | 8 | 35 |
| 14 | 9 | 4 | 6 | 6 | 8 | 29 |
| 15 | 6 | 3 | 6 | 5 | 6 | 29 |
| 16 | 9 | 4 | 8 | 6 | 8 | 35 |
| 17 | 8 | 4 | 7 | 6 | 9 | 34 |
| 18 | 7 | 3 | 6 | 5 | 7 | 28 |
| 19 | 10 | 4 | 7 | 8 | 8 | 37 |
| 20 | 11 | 5 | 6 | 8 | 7 | 37 |
| 21 | 8 | 4 | 7 | 7 | 9 | 35 |
| 22 | 13 | 5 | 8 | 9 | 10 | 45 |
| ድምር | 203 | 86 | 159 | 155 | 178 | 779 |
| አማካይ ውጤት | 9.22 | 3.90 | 7.22 | 7.04 | 8.09 | 35.40 |

ለ. የአማርኛ ቋንቋ አፊ-ፊት ተማሪዎች የፈተና ሁለት ውጤት

| ተ.ቁ | የምርጫ ጥያቄ (15%) | ቃላትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎ (5%) | ሰርዓታቸውን የጠበቁ ሰዋሰዋዊ ዓረፍተ ነገሮች መመስረት(10%) | የሐረጎች መሪ ቃላትና የሐረጎችን አይነት መፃፍ(10 %) | እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍቺ መስጠት (10%) | የፈተና ሁለት ድምር ውጤት (10%) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 10 | 4 | 9 | 8 | 9 | 40 |
| 2 | 9 | 4 | 8 | 8 | 8 | 37 |
| 3 | 11 | 5 | 7 | 9 | 10 | 42 |
| 4 | 7 | 4 | 6 | 8 | 8 | 33 |
| 5 | 12 | 5 | 9 | 10 | 10 | 46 |
| 6 | 10 | 4 | 8 | 8 | 9 | 39 |
| 7 | 9 | 4 | 8 | 7 | 8 | 36 |
| 8 | 7 | 3 | 7 | 8 | 7 | 32 |
| 9 | 8 | 4 | 7 | 7 | 8 | 34 |
| 10 | 10 | 4 | 8 | 8 | 9 | 39 |
| 11 | 12 | 5 | 9 | 9 | 10 | 45 |
| 12 | 10 | 4 | 7 | 8 | 9 | 38 |
| 13 | 9 | 3 | 8 | 8 | 9 | 37 |
| 14 | 9 | 4 | 8 | 8 | 7 | 36 |
| 15 | 7 | 3 | 7 | 6 | 8 | 31 |
| 16 | 9 | 4 | 7 | 8 | 9 | 37 |
| 17 | 10 | 4 | 8 | 9 | 10 | 41 |
| 18 | 8 | 3 | 7 | 7 | 8 | 33 |
| 19 | 8 | 4 | 8 | 8 | 7 | 35 |
| 20 | 7 | 5 | 6 | 7 | 8 | 33 |
| 21 | 10 | 4 | 7 | 9 | 9 | 39 |
| 22 | 13 | 5 | 10 | 10 | 10 | 48 |
| ድምር | 205 | 89 | 164 | 178 | 190 | 831 |
| አማካይ ውጤት | 9 | 34.04 | 7.45 | 8.09 | 8.63 | 37.77 |

የፈተናዎች ዉጤት

ሀ. የጉራጊኛ  ቋንቋ አፈ-ፈት ተማሪዎች የፈተና አንድ ውጤት

| ተ.ቁ | የምርጫ ጥያቄ (15%) | ቃላትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች (5%) | ስርዓታቸውን የጠበቁ ሰዋሰዋዊ ዓረፍተ ነገሮች መመስረት(10%) | የሐረጎች መሪ ቃላትና የሐረጎችን አይነት መፃፍ (10%) | እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍቺ መስጠት (10%) | የፈተና አንድ ድምር ውጤት (10%) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 12 | 5 | 8 | 7 | 8 | 38 |
| 2 | 7 | 2 | 7 | 6 | 6 | 29 |
| 3 | 8 | 4 | 6 | 7 | 8 | 33 |
| 4 | 6 | 3 | 6 | 5 | 6 | 26 |
| 5 | 9 | 4 | 7 | 7 | 8 | 35 |
| 6 | 7 | 3 | 8 | 6 | 7 | 31 |
| 7 | 10 | 4 | 7 | 7 | 8 | 36 |
| 8 | 9 | 4 | 6 | 6 | 7 | 32 |
| 9 | 7 | 3 | 6 | 5 | 5 | 26 |
| 10 | 9 | 4 | 6 | 5 | 6 | 30 |
| 11 | 8 | 3 | 5 | 6 | 7 | 29 |
| 12 | 9 | 3 | 7 | 6 | 8 | 33 |
| 13 | 8 | 4 | 7 | 7 | 8 | 34 |
| 14 | 7 | 3 | 8 | 6 | 7 | 31 |
| 15 | 9 | 4 | 7 | 6 | 8 | 34 |
| 16 | 8 | 4 | 7 | 6 | 6 | 31 |
| 17 | 10 | 5 | 8 | 8 | 9 | 40 |
| 18 | 9 | 4 | 8 | 7 | 7 | 35 |
| 19 | 8 | 3 | 7 | 6 | 7 | 31 |
| 20 | 10 | 4 | 8 | 7 | 8 | 37 |
| 21 | 7 | 3 | 6 | 6 | 8 | 30 |
| 22 | 9 | 4 | 8 | 7 | 7 | 35 |
| 23 | 9 | 3 | 6 | 7 | 8 | 33 |
| 24 | 8 | 3 | 8 | 7 | 7 | 33 |
| 25 | 7 | 3 | 7 | 6 | 6 | 29 |
| 26 | 6 | 2 | 5 | 5 | 6 | 24 |
| 27 | 7 | 3 | 6 | 6 | 7 | 29 |
| 28 | 8 | 4 | 7 | 7 | 8 | 34 |
| ድምር | 230 | 98 | 186 | 177 | 201 | 889 |
| አማካይ ውጤት | 8.21 | 3.5 | 6.64 | 6.32 | 7.17 | 32.07 |

ለ. የጉራጊኛ  ቋንቋ አፌ-ፊት ተማሪዎች የፈተና ሁለት ውጤት

| ተ.ቁ | የምርጫ ጥያቄ (15%) | ቃላትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች (5%) | ሰርዓታቸውን የጠበቁ ሰዋሰዋዊ ዓረፍተ ነገሮች መመስረት(10%) | የሐረጎች መሪ ቃላትና የሐረጎችን አይነት መፃፍ (10%) | እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍቺ መስጠት (10%) | የፈተና ሁለት ድምር ውጤት (10%) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 11 | 4 | 9 | 8 | 10 | 42 |
| 2 | 8 | 3 | 7 | 6 | 7 | 31 |
| 3 | 9 | 4 | 8 | 8 | 9 | 38 |
| 4 | 6 | 3 | 7 | 7 | 8 | 31 |
| 5 | 9 | 4 | 7 | 8 | 8 | 36 |
| 6 | 7 | 3 | 6 | 7 | 7 | 30 |
| 7 | 10 | 5 | 9 | 8 | 9 | 41 |
| 8 | 9 | 4 | 8 | 7 | 8 | 36 |
| 9 | 7 | 3 | 6 | 7 | 8 | 31 |
| 10 | 9 | 4 | 7 | 6 | 9 | 35 |
| 11 | 8 | 3 | 7 | 8 | 7 | 33 |
| 12 | 10 | 3 | 8 | 9 | 10 | 40 |
| 13 | 8 | 4 | 7 | 8 | 9 | 36 |
| 14 | 7 | 5 | 6 | 7 | 8 | 33 |
| 15 | 9 | 4 | 8 | 8 | 8 | 37 |
| 16 | 8 | 4 | 8 | 7 | 7 | 34 |
| 17 | 10 | 5 | 9 | 8 | 9 | 41 |
| 18 | 9 | 4 | 8 | 9 | 8 | 38 |
| 19 | 8 | 3 | 6 | 8 | 9 | 34 |
| 20 | 9 | 4 | 8 | 7 | 7 | 35 |
| 21 | 7 | 3 | 5 | 8 | 7 | 30 |
| 22 | 9 | 4 | 8 | 6 | 8 | 35 |
| 23 | 9 | 3 | 9 | 7 | 8 | 36 |
| 24 | 8 | 3 | 7 | 8 | 7 | 33 |
| 25 | 7 | 3 | 8 | 8 | 6 | 32 |
| 26 | 6 | 2 | 7 | 6 | 6 | 27 |
| 27 | 7 | 3 | 8 | 8 | 8 | 34 |
| 28 | 8 | 4 | 7 | 9 | 87 | 35 |
| ድምር | 232 | 101 | 208 | 211 | 221 | 974 |
| አማካይ ውጤት | 8.28 | 3.60 | 7.42 | 7.53 | 7.92 | 34.78 |

የፈተናዎች ዉጤት

ሀ. የኦሮምኛ ቋንቋ አፊ-ፊት ተማሪዎች የፈተና አንድ ውጤት

| ተ.ቁ | የምርጫ ጥያቄ (15%) | ቃላትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች (5%) | ሰርዓታቸውን የጠበቁ ሰዋሰዋዊ ዓረፍተ ነገሮች መመስረት(10%) | የሐረጎች መሪ ቃላትና የሐረጎችን አይነት መፃፍ (10%) | እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍቺ መስጠት (10%) | የፈተና አንድ ድምር ውጤት (10%) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 10 | 4 | 7 | 5 | 6 | 32 |
| 2 | 8 | 4 | 6 | 7 | 6 | 31 |
| 3 | 6 | 3 | 6 | 5 | 5 | 25 |
| 4 | 7 | 3 | 5 | 6 | 6 | 27 |
| 5 | 10 | 5 | 8 | 7 | 6 | 36 |
| 6 | 8 | 3 | 7 | 5 | 6 | 29 |
| 7 | 9 | 3 | 8 | 6 | 5 | 32 |
| 8 | 7 | 4 | 7 | 4 | 6 | 27 |
| 9 | 7 | 3 | 7 | 5 | 7 | 30 |
| 10 | 9 | 4 | 8 | 6 | 7 | 34 |
| 11 | 8 | 4 | 7 | 7 | 8 | 35 |
| 12 | 9 | 5 | 6 | 6 | 7 | 31 |
| 13 | 10 | 3 | 9 | 7 | 8 | 38 |
| 14 | 7 | 4 | 7 | 5 | 6 | 28 |
| 15 | 9 | 3 | 7 | 7 | 7 | 33 |
| 16 | 9 | 4 | 6 | 6 | 7 | 34 |
| 17 | 8 | 3 | 5 | 7 | 8 | 31 |
| 18 | 7 | 3 | 5 | 6 | 7 | 28 |
| 19 | 9 | 3 | 8 | 7 | 8 | 37 |
| 20 | 8 | 3 | 6 | 8 | 7 | 29 |
| ድምር | 165 | 71 | 135 | 119 | 133 | 625 |
| አማካይ ውጤት | 8.25 | 3.55 | 6.75 | 5.95 | 6.65 | 31.25 |

የፈተናዎች ዉጤት

ለ. የኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ተማሪዎች የፈተና ሁለት ውጤት

| ተ.ቁ | የምርጫ ጥያቄ (15%) | ቃላትን የሚመለከ ቱ የተለያዩ ጥያቄዎች (5%) | ሰርዓታቸውን የጠበቁ ሰዋሰዋዊ ዓረፍተ ነገሮች መመስረት(10%) | የሐረጎች መሪ ቃላትና የሐረጎችን አይነት መፃፍ (10%) | እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍቺ መስጠት (10%) | የፈተና ሁለት ድምር ውጤት (10%) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 9 | 4 | 7 | 6 | 8 | 34 |
| 2 | 11 | 5 | 6 | 7 | 9 | 38 |
| 3 | 9 | 3 | 5 | 6 | 8 | 31 |
| 4 | 7 | 4 | 6 | 6 | 7 | 30 |
| 5 | 10 | 5 | 8 | 7 | 9 | 39 |
| 6 | 7 | 4 | 7 | 6 | 7 | 31 |
| 7 | 8 | 4 | 8 | 7 | 8 | 35 |
| 8 | 9 | 4 | 7 | 7 | 8 | 35 |
| 9 | 7 | 3 | 7 | 7 | 8 | 32 |
| 10 | 12 | 5 | 8 | 7 | 9 | 41 |
| 11 | 8 | 4 | 6 | 7 | 8 | 33 |
| 12 | 7 | 3 | 7 | 6 | 8 | 31 |
| 13 | 8 | 4 | 8 | 8 | 7 | 35 |
| 14 | 9 | 4 | 7 | 6 | 8 | 34 |
| 15 | 8 | 3 | 7 | 8 | 9 | 35 |
| 16 | 7 | 2 | 6 | 7 | 8 | 30 |
| 17 | 9 | 4 | 5 | 7 | 8 | 33 |
| 18 | 10 | 3 | 5 | 8 | 9 | 35 |
| 19 | 9 | 4 | 8 | 7 | 8 | 36 |
| 20 | 10 | 4 | 6 | 7 | 8 | 35 |
| ድምር | 174 | 76 | 134 | 137 | 154 | 683 |
| አማካይ ውጤት | 8.7 | 3.8 | 6.7 | 6.85 | 7.7 | 34.15 |

የፈተናዎች ዉጤት

ሀ. የከንባትኛ ቋንቋ አፊ-ፊት ተማሪዎች የፈተና አንድ ውጤት

| ተ.ቁ | የምርጫ ጥያቄ (15%) | ቃላትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች (5%) | ስርዓታቸውን የጠበቁ ሰዋሰዋዊ ዓረፍተ ነገሮች መመስረት(10%) | የሐረጎች መሪ ቃላትና የሐረጎችን አይነት መፃፍ (10%) | እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍቺ መስጠት (10%) | የፈተና አንድ ድምር ውጤት (10%) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 8 | 4 | 8 | 6 | 7 | 33 |
| 2 | 10 | 4 | 8 | 8 | 9 | 39 |
| 3 | 9 | 4 | 6 | 8 | 8 | 36 |
| 4 | 6 | 3 | 7 | 4 | 6 | 26 |
| 5 | 11 | 5 | 8 | 7 | 8 | 39 |
| 6 | 7 | 4 | 8 | 5 | 6 | 30 |
| 7 | 9 | 4 | 7 | 5 | 5 | 30 |
| 8 | 6 | 2 | 5 | 4 | 5 | 22 |
| 9 | 7 | 4 | 6 | 7 | 8 | 32 |
| 10 | 12 | 5 | 8 | 8 | 9 | 42 |
| ድምር | 85 | 39 | 71 | 62 | 71 | 328 |
| አማካይ ውጤት | 8.5 | 3.9 | 7.1 | 6.2 | 7.1 | 32.8 |

የፈተናዎች ዉጤት

ለ. የከንባትኛ ቋንቋ አፊ-ፊት ተማሪዎች የፈተና ሁለት  ውጤት

| ተ.ቁ | የምርጫ ጥያቄ (15%) | ቃላትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች (5%) | ሰርዓታቸውን የጠበቁ ሰዋሰዋዊ ዓረፍተ ነገሮች መመስረት(10%) | የሐረጎች መሪ ቃላትና የሐረጎችን አይነት መፃፍ (10%) | እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍቺ መስጠት (10%) | የፈተና ሁለት ድምር ውጤት (10%) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 8 | 4 | 8 | 6 | 7 | 33 |
| 2 | 10 | 4 | 8 | 8 | 9 | 39 |
| 3 | 9 | 4 | 6 | 8 | 8 | 36 |
| 4 | 6 | 3 | 7 | 4 | 6 | 26 |
| 5 | 11 | 5 | 8 | 7 | 8 | 39 |
| 6 | 7 | 4 | 8 | 5 | 6 | 30 |
| 7 | 9 | 4 | 7 | 5 | 5 | 30 |
| 8 | 6 | 2 | 5 | 4 | 5 | 22 |
| 9 | 7 | 4 | 6 | 7 | 8 | 32 |
| 10 | 12 | 5 | 8 | 8 | 9 | 42 |
| ድምር | 85 | 39 | 71 | 62 | 71 | 328 |
| አማካይ ውጤት | 8.5 | 3.9 | 7.1 | 6.2 | 7.1 | 32.8 |